ታህሳስ 2014
ቅጽ ፩ ቁጥር ፫


# ንስንስ

ትኩረቷን በLBTQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ የምትታተም መጽሔት
Nisnis - quarterly magazine focusing on LBTQ issues



# ማንነትን መግለጥ

አታሚ/Publisher
QUEER ETHIOPIA
ኲዊር ኢትዮጵያ




# የራስዎን ድምፅ ያድምጡ

www.soundcloud.com/ethioqueer

# ንስንስ

ቅጽ ፩ ቁጥር ፫

በየሩብ ዓመቱ የምትታተመው ንስንስ
በኢትዮጵያ እና በዳያስፖራ የሚገኙ LBTQ
ጉዳዮች ላይ የምታተኩር መጽሄት ናት።

ለጥያቄዎች :
etqueerfamily@gmail.com

በኩዊር ኢትዮጵያ የታተመ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
© ታህሳስ 2014

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| 3 | የአርታዒያን መልዕክት |
| 4 | የብርታት ገጽታ |
| 21 | ራስን መግለጥ፥ በስራ ላይ |
| 22 | የፍርድ ቀን |
| 26 | ራስ መቀበልን ማሳድግ |
| 30 | ሀዘን እና በዐል |
| 34 | ምቹ ቁምሳጥን |
| 37 | የኩዊር አጋር ማስታወሻ |
| 40 | ፍቅር፣ ማንነትን ማሳበቅ እና ፍርሃት |
| 43 | ቤተሰባችሁ ማንነታችሁን ብትገልፁላቸው ምን ይላሉ? |
| 46 | ምስጋና ለቤተሰብ |




# QUEER ETHIOPIA

# ኩዊር ኢትዮጵያ

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኽውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ' ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።


queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com


ንስንስ | ታህሳስ 2014

# የአርታዒያን መልዕክት

እንኳን ወደ ንሥንሥ ሦስተኛ ኅትመት በደኽና መጡ፤ እስካሁንም ጊዜ ወስዳችሁ መጽሔታችንን እያነበባችሁ ስለሆነ እናመሰግናለን።

በዚኽ ኅትመታችን ትኩረታችንን ያደረግነው ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ስለማድርግ ሲሆን፤ ይኽንንም ርዕስ ልንመርጥ የወደድነው በ“LBTQ” ማኅበረሰብ ውስጥ ፋይዳው ጉልኽ በመሆኑ ምክንያት ነው። ራሳችንን “በኩዊር” ሥፍራ ስናገኘው የሚነሣ ተደጋጋሚ ጥያቄ “እንዴት ነበር ወሲባዊ ማንነትሽን ግልጽ ያደረግሽበት ሂደት?” የሚለው በተወሠነ ደረጃ መለያየቱ ነው። ይኽን ጥያቄ ጠቃሚ የሚያደርገው የሆነ ዓይነት ተሞክሮ በማጋራት ረገድ በር ከፋች ስለሆነ ብቻ ሣይሆን፤ እንደ “ኩዊር” ሰው ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድረግ በሕይወታችን ትርጉም ያለው ሁነት በመሆኑ ምክንያት ጭምር ነው።

ይኽ ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድረግ የግድ የሚል መሆኑን ለመጠቆም ወይም የአንድ ጊዜ ተግባርና ሁነት ሆኖ አይደለም። ይልቅም፤ ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድረግ መቻል እያንዳንዳችን በልዩ ሁኔታ ትርጉም የምንሰጠውና የምንተገብረው የማያቆም ጉዞ በመሆኑ ነው። ለአብዛኛዎቻችን ኢትዮጵያዊያን በወሲባዊ ማንነታችን ወይም በፆታዊ ማንነታችን የተነሣ ዋጋ እንደሌለን እንዲሰማን እየተማርን ላደግን፤ ራስን የመቀበሉ ጎዳና ብዙውን ጊዜ ራስን መጠራጠር ያለበት፣ ለራስ ጥላቻ እና እንደቤታችን ሊሰማን ከሚገባው የመነጠል ስሜት የሚፈጥር ሕመም የተሞላ ነው።

በሰዓቱ ሥቃዩ እጅግ ሕመም ያለው፤ በቃለ-መጠይቅ መኻል እንኳን ሰዎች ተደላድለው ንግግራችንን ሊቀጥሉ ሲሉ እስክናቆም የምንሆንበት ነው። ወሲባዊ ማንነታችንን ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ግልጽ ያደረግንበት ትዝታው እንኳን ከባድና ሕመም ያለው ነው።

“በ’ኔ፣ በቤተሰቤና በእኛ ማኅበረሰብ መካከል መጥፎ ጊዜ የነበረ በመሆኑ ምክንያት ስለዛን ወቅት ጨርሶ አናወራም።” ትላለች ሚኬሊና ዮናስ በላይነህ ራስን የመቀበል ትግላቸውን ስታስታውሰው። በኋላ ላይ ያገኙት ተቀባይነት አነቃቂ የነበረ ቢሆንም እዛ ለመድርስ ያሳለፉት ሥቃይ ግን አብዛኞቻችን የምንጋራው ነገር ነው።

ማኅበር መፍጠርም ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ በማድረግ ጉዞ ያለውን ጠቀሜታ ጭምር ተምረንበታል። በትንሽ የክልል ርዕሰ-ከተማ ያደገችው ሌዝቢያኗ ዮርዳኖስም ራሷን መቀበሏ በማኅበራዊ ትሥሥር ገጽ አማካኝነት ከ“LGBTQ+” ማኅበረሰብ ጋር መፍጠር የቻለችው ግንኙነት ውጤት እንደሆነ ትገልጻለች።

ብሌን በበኩላቸው በራሳችን ማኅበር ውስጥ ያለውን ግርታ ለማጥራትም አንዳችን ሌላኛችንን መሞገት እንዳለብን ያስታውሳሉ። “ትራንስፎቢያ” ፥ የተለያዩ ስርዕተ ፆታና ወሲባዊ ማንነት ያላቸው ሰዎች ማንነታቸውን ግልጽ ሲያደርጉ በ“LBTQ” ማኅበረሰብ ውስጥ ሳይቀር የሚጋፈጡት ተግዳሮት አፋጣኝ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው። እነሱ እንደሚሉት “በማኅበረሰባችን ውስጥ አንዳች ዓይነት አስተምህሮ ተፈጠሮ ማየት ቢቻል ቆንጆ ይሆናል፤ ምክንያቱም ያ ነው የጎደለን ነገር።”

በአንዳንዶች ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ላለማድረግ የመምረጡ ሃሳብም በራሱ እንደ ዐብዮት የሚቆጠር ነው። ምክንያቱም ለራስ ማሰብ ወሣኝ እንደሆነ ስለሚያሳይ፤ ከመሞት መሰንበት ነውና ኢትዮጵያን እንደ “ኩዊር” ሰው ለማሰስም አስፈላጊው ነገር ነው። ግልጽ ስንወጣ፤ ወሲባዊ ማንነታችንን ግልጽ ስናደርግ ጓደኞቻችንን እና የምንወዳቸውን የማጣት ኃላፊነት መውሰድም ይጠይቃል፤ በሌላ መልኩ ባልተለመዱ ቦታዎች የምናገኛቸው አጋርነትም በዚኽ ኅትመታችን ከሚዳሰሱ ጉዳዮች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው።

እነዚኽ እንደ ኢትዮጵያዊና ኤርትራዊ የዘር-ግንድ እንዳለው የ“LBTQ” ሰዎች  ወሲባዊ ማንነታችንን ግልጽ ማድረግን የተመለከቱ ስብስብ ታሪኮቻችን ናቸው። ሁላችንም የብርታት ገጽታዎች ነን። የራሳችንን ታሪክ የመጻፋችን ዕውነት ትልቅ ዐሻራ ነው።  ምናልባትም ጉዞው ረጅም ወይም መቼም የማያልቅ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ትንሿን ዕርምጃ መጀመራችን ሊያስመሰግነን ይገባል፤ ምክንያቱም መክሊት ሞሪስን በግጥሟ ላይ እንደጻፈችው “ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድረግ”፣ “በቂ ነው/ኀልው ለመሆን/በጉልህ “ኩዊር” ለመሆን”።

እንደሁልጊዜው ሁሉ፤ በዚኽችኛ መጽሔታችን የኅትመት ሂደት ለተሣተፋችሁ ሁሉ እናመሰግናለን። ቀጣይነት ያለው ድጋፋችሁ ለሁሌውም ጠቃሚ ለሆነው አካታች እና ተራማጅ የ“LBTQ” ማኅበረሰብ ለመገንባት ላለብን ኃላፊነት ይረዳናል።

መልካም ንባብ ይሁንላችሁ!

# የብርሃን ገጽታ

## ኩዊርነትን በጀግንነት መኖር

ዮሃና ፣ ሚከሊና ፣ ዮርዳኖስ እና ብሌን ኲዊር ትውልደ ኢትዮጵያዊ (ኤርትራዊ) ናቸው። ንስንስ ማንነታቸውን ለራሳቸው እና ለሌሎች በመግለጥ ዙሪያ ያላቸውን ጉዞ አነጋግራቸዋለች።


# ዮሃና

በኢትዮጵያ የክልል መቀመጫ በሆነች ከተማ የተወለደችው "ሌዝቢያን" ዮሃና ወሲባዊ ማንነቷን ለመጀመሪያ ጊዜ ግልጽ ያደረገችበትን አስቂኝ አጋጣሚ ታስታውሰዋለች።

"መጀመሪያ የነገርኩት ሰው 'ኦንላየን' ላይ ላለ ጓደኛዬ ነበር። መጀመሪያ 'ይመስለኛል 'ባይሴክሹዋል' ነኝ' ነበር ያልኩት። እንደዛ ያልኩት ያው እንደወንድ ሊጠላኝ የሚችልበትን ዕድል ለመቀነስ ብዬ በማሰብ ነው። በቀልድ ነበር ምላሽ የሰጠኝ 'ያ ማለት ሁለት ሲም ነው የምትወስጂው ማለት ነው?' በማለት"

ዮሃና እንደምትለው መጀመሪያ ወሲባዊ ማንነቷን ግልጽ ያደረገችለት ሰው ነገሩን ቀለል አድርጎና ምንም ማለት እንዳልሆነ አድርጎ መውሰዱ ስለማንነቷ የበለጠ ለማወቅ እንድትጥር እንዳበረታታት ትናገራለች።

የዮሃና ስለወሲባዊ ተማርኮዋ ለማወቅ ጥረት ማድረግ የጀመረችው ገና ወጣት ሳለች ነበር። ከጓደኞቿ ለአንዷ ኃያል ፍቅር ነበራት፤ እናም ይህ ስሜቷ ወሲባዊ ተማርኮ ያላት ለሴት ነው ማለት ይሆን ወይስ ወይስ ጓደኛዋን የወደደችበት ከወሲባዊ ተማርኮ ውጪ ነው የሚለው



ግልጽ አልነበረም።

“ጨርሶ በተለየ ዓለም ውስጥ ነበርኩ” ትላለች። “በርግጥ አሁን ላይ ሆኜ ራሴን ስጠይቅ፤ ራሴን እንደወንድ ነበር የማየው መሰለኝ፤ ከማንነት ጋር አላገናኘውም ነበር። አገናኘው የነበረው ለሷ ካለኝ ፍቅር ጋር ብቻ ነበር።”

ዮሃና ለሴት ጓደኛዋ ያላትን ተማርኮ ከወሲባዊ ተማርኮዋ ጋር የማይገናኝ ነገር አድርጋ ነበር ያስተናገደችው። በርግጥ ስለወሲባዊ ተማርኮዋና ማንነቷ ማሳብና ለማወቅ መጣር የጀመረችው ለጓደኛዋ የነበራት ፍቅር ካበቃ በኋላ ነበር። እንዲህ ብላ ስም ለመስጠት ቋንቋ ቢቸግራትም፤ ያኔ ነው ለሌሎች ሴቶችም ፍቅር ተሰምቷት እንደሚያውቅ ማሰብ የቻለችው።

በመጨረሻም ስለወሲባዊ ተማርኮዋ ለማወቅ ዝግጁ ሆነች፤ እናም “ጎግልን” የመጀመሪያ የማወቂያ አማራጯ አደረገች።

“ይመስለኛል የመጀመሪያ ቀን ‘ሌዝቢያን’ የሚለውን ቃል ‘ጎግል’ ያደረኩበት ቀን ስለማንነቴ የተቀበልኩበት ቀን ነው። ያው ስሜት እንዳለሽ ታውቂዋለሽ ነገር ግን ከዛ በፊት ልትቀበይው አትፈልጊም፤ ምክንያቱም ከባድ ሆኖ ታገኚዋለሽ።” ትላለች ዮሃና።


“‘ሌዜቢያን’ ነኝ?” የሚለውንና በማስከተልም “ሌዜቢያን መሆን ኃጢያት ነው?” ብላ ጎግል አደረገች፤ ያገኘቻቸው የተወሡኑት መልሶች በአጽንዖት ኃጢያት መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው፤ እናም ሁኔታው ኃይማኖታዊ ሥረ-መሠረቷ ተጨምሮበት ወደመጠራጠርና የጥረቷ እንቅፋት ወደ’መሆን አመራ። ያም ሆኖ ግን ከማንነቷ መደበቅ ከባድ ሆኖ አግኝታዋለች፥ እናም በጽናት ስለስሜቷና ተማርኮዋ መልስ ለማግኘት መጣሯን ቀጠለች።

ያም ብቻ አይደለም “ከጎግል ፕለይ” ላይ ስለማንነቷ አስተያየት ሊሰጧት የሚችሉና ወሲባዊ ተማርኮዋ ወዴት እንደሆነ ለማወቅ የጀመረችውን ጥረት ሊረዱ የሚችሉ “አፖችን” ማውረድ ጀመረች። ምንም እንኳን ዮሃና ብዙ ዓይነት “አፖችን” ብታገኝም ለምዕራቡ ዓለም ታስበው እንደመዘጋጀታቸው መጠን ከራሷ ጋር ማነጻጸር ከባድ ሆኖ አገኘችው። የፍቅር አጣማሪዋን “በአፖቹ” አማካኝነት ለማግኘት ብትጥርም አፖቹ እንዳሰበችው ሆነው ባታገኛቸውም፤ ራሷን እንድትቀበል ግን ትልቅ ሚና ተጫውተዋል።

ራሷን ለማወቅ ከረዷት መካከል የኢንተርኔት ጥያቄዎች አንዱ ነው።

“ ‘ሌዜቢያን ነኝ?’ የሚል የኢንተርኔት ጥያቄ ጨዋታ አገኘሁኝ እናም ተጫወትኩት” ትላለች ዮሃና “ምላሹ ትልቅ ፐርሰንት ነበር ያገኘሁት እናም በርግጥም እኔ ሌዝቢያን መሆኔን አረጋገጠልኝ።”

> **ይመስለኛል የመጀመሪያ ቀን ‘ሌዝቢያን’ የሚለውን ቃል ‘ጎግል’ ያደረኩበት ቀን ስለማንነቴ የተቀበልኩበት ቀን ነው።**
>
> ዮሃና



"ጎግል" ላይ ባገኘችው መልስና በጥያቄው ላይ ባስቆጠረችው ውጤት የተነሳ ዮሃና ራሷን መቀበል ችላለች፤ ከዛ በኋላ ያለው ብቸኛው ጭንቀቷ እንዴት አድርጌ ሌላ "ኩዊር" ሰዎች አገኛለሁ የሚለው ነበር። ቁርጠኝነቱን ባታጣውም ኢትዮጵያ ውስጥ "LGBTQ+" ሰዎችን ለመፈለገግ ፍርኃት ነበራት።

"ያስፈራሻል፤ በጣም ያስፈራሻል፤ ዐይቶሽ ብቻ ማንም 'ሌዝቢያን' እንደሆንሽ ማወቅ የሚችል ይምስልሻል። አንዳንድ "ጊዜያት አሉ ለሁሉም ሰው መንገር የምትፈልጊበት፤ ጮክ ብለሽ መናገር..." ትላለች ዮሃና።

ራሷን ከተቀበለች ብዙም ሳይቆይ ለተወሠኑ ሰዎች ለመንገር ሞክራለች። ከነዚህም ውስጥ "ዴት" ሊያደርጋት የሚፈልግ ሰው ነበር። እናም ስለወሲባዊ ማንነቷ ስትነግረው እንደተሳሳተች፤ ጭንቀት የፈጠረው እንደሆነና ይህ አንዱ መገለጫው እንደሆነ "ከሌዝቢያንነቷ" እንድትመለስም ሊረዳት እንደሚችል ነገራት።

አሁን ላይ የሚያስቃት ነገር ቢሆንም፤ በሰዓቱ "መቀየር" ትፈልግ ስለነበር ባቀረበው መከራከሪያ ወደማመኑ ደርሳ ነበር፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ "ሌዝቢያን" መሆን ሕይወትን ምን ያህል ሊያከብድ እንደሚችል ስለምታውቅ "ሌዝቢያን" መሆን አትፈለግም ነበር። ሌላ የነገረችው ሰው ደ'ሞ "ከሌዜቢያንነት" ለመገላገል መጠመቅ እንዳለባት ነገራት።

ራሷን ለመቀበል ሌላው ጫና የፈጠረባት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ማደጓ ነበር። ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነትን የሚጻረሩ ተደጋጋሚ ስብከቶች በቤተ-ክርስቲያን መስማቷ ራሷን እንድትጠይቅ አድርጓታል።

"የኔ በቤተ-ክርስቲያን መገኘት በ'ግብር-ሰዶም' (በቀጥታ ትርጉሙ 'የሰዶም ሥራ') የሚጻረሩ ስብከቶች የሚስብ አንዳች ነገር ያለው ይመስላል እና ሰዶም ደ'ሞ ሁሉም ነገር እንዲጠፋ የሆነበት ጊዜ ነበር" ትላለች ዮሃና። "እየደጋገሙ የፍርድ ቀን መቅረቡን ይናገራሉ እናም ራሴን እስክጠላ ፍርኃት ፈጠረብኝ።"

ብቸኛ "LGBTQ+" የመሆን ስሜቱ በራሱ ራሷን እንደ "ሌዜቢያን" መቀበሉን ከባድ አድርጎታል።

"እንደኔ ካሉት ሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጥሩ ከባድ ነበር፤ ያ ደ'ሞ ብቸኝነት እንዲሰማኝ ያደርገኝ ነበር። 'ያልተለመደ' ዓይነት ሰው በመሆኔ ራሴን እወቅሰው ነበር። ራሴን 'ለምንድን ነው እንደሌሎች ሴቶች 'ኖርማል' መሆን ያልቻልኩትና ወንድ ወድጄ ቤተሰቦቼን ደስተኛ ማድረግ ያቃተኝ?' እያልኩ እጠይቀው ነበር።" ትላለች።

ዮሃና ያፈቀረቻት ልጅ ብትቀበላትና በትምህርት ቤት ላለው ሁሉና ለማኅበረሰቡ እናገራለሁ ብላ የምታስፈራራት ባትሆን ኖሮ ወሲባዊ ማንነቷን ግልጽ የማድረጉ ጉዳይ ቀላል ይሆንላት እንደነበር ታምናለች። ያ ተሞክሮዋ ምክንያት ሆኗት "LGBTQ+" ካልሆኑ ሰዎች ጋር ጓደኝነት የመሥረቱ ጉዳይ ከባድ ሆኖ እንዳገኘችው ትናገራለች።

ከተሞክሮዋ አንጻር ለሌሎች ራሳቸውን ግልጽ ለማድረግ ለሚፈልጉ የምትመክረው ነገር ቢኖር ለማን እንደሚነግሩ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ነው። ሰዎች ለሌሎች ራሳቸውን ግልጽ ከማድረጋቸው በፊት የሌላኛው ሰው ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰላት እንዳለባቸው ታምናለች።

"ራስን ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነው በእውነትም ላንቺ አስፈላጊ ለሆኑ ሰዎች ብቻ ነው።" ትላለች ዮሃና። "ቆይ አንድ ሰው መጥቶ "ስትሬት" ነኝ ይልሻል? ሕይወታቸውን እንደ 'ኖርማል' ዝም ብለው ነው የሚኖሩት እናም እንደ 'ስትሬት' ራሳቸውን ግልፅ ማድረግ አይጠበቅባቸውም። ስለዚህ እኛም ራሳችንን ግልጽ የማድረግ ግዴታ የሉብንም። በርግጥ ሕይወታችንን እንደዛ መኖር ብንችል እመኛለሁ፤ ስለራስሽ ሕይወት ማብራራት ሳይጠበቅብሽ ሴት 'ዴት' ማድረግ መቻል።"

> "ራሴን 'ለምንድን ነው እንደሌሎች ሴቶች 'ኖርማል' መሆን ያልቻልኩትና ወንድ ወድጄ ቤተሰቦቼን ደስተኛ ማድረግ ያቃተኝ?' እያልኩ እጠይቀው ነበር።" ትላለች።
>
> ዮሃና

# ሚኬሊና

“ልጄ “ጌ” ናት፤ ልደብቀው የምችለው ነገር አይደለም ምክንያቱም ምንም ዓይነት ነገር አያሳፍረንም። ሰዎች ልጄ “ኲዊር” በመሆኗ ምክንያት ከእኛ ወይም ከእኔ ሕይወት ውስጥ መውጣት ቢፈልጉ አልጠላቸውም፤ ግምት ልወስድባቸውም አልፈልግም፤ ነገር ግን ልጄን እንደማንነቷ ሊቀበሏት ካልቻሉ እነሱም በኛ ሕይወት ውስጥ ቦታ እንደሌላቸው እነግራቸዋለሁ።” እናታቸው ወሲባዊ ማንነታቸውን ግልጽ በማድረግ ጉዞዋቸውን አስመልክቶ የተናገሩትን ቃል ሚኬሊና ዮናስ ያስታውሳሉ።

ሚኬሊና ቤተሰባቸው ከኢትዮጵያ እና ከኤርትራ የሆኑ የ”ኲዊር” እና “ፍሉድ ነንባይነሪ” የመጀመሪያ ትውልድ አሜሪካዊ ናቸው። ሚኬሊና ያደጉት በማኅበራዊ ሕይወቱና በባህሉ በተሳሰረ እንዲሁም በምሥራቅ አፍሪካ ካሉ ዘር’ማንዘሮቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ካላቋረጡ በአያት ቅድም አያቶቻቸው በተከበበ ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። ልጆቻቸውን የራሳቸው የሆነውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ አስተምረዋቸዋል፤ የራሳቸው የሆነም ማኅበር እንዲሁም የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን አቋቁመዋል። በዛ የተነሣ ሚኬሊና ደንበኛ የሐበሻ ቤተሰብ ወይም ማኅበረሰብ እንደነበሩ ይናገራሉ።

የሚኬሊና ራሳቸውን የመሰየም ረጅም ጉዞ (አሁንም በሂደት ላይ ያለ ነው) የጀመረው እዚሁ ማኅበረሰብ ውስጥ ነው።

“እንደ’ልጅ የመጀመሪያ ትዝታዬ ልክ ያለመሆን ስሜት እንደነበር ትዝ ይለኛል። ለተመሳሳይ ፆታ መማረክ ሲሰማኝ አስታውሳለሁ። ለወንድ ተማርኬ እንደማላውቅ አላውቅም ነበር ፤ ግን ሃሳብ ብቻ ነው፤ ነገሮች ከሚጠበቅባቸው መስመር የወጡ፥ መሆን የሚጠበቅብኝና እኔ መሆን የነበረብኝ...” ይላሉ።

ጉዟቸውን የበለጠ ለማስፋት፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ አለመሆናቸው ከወሲባዊ ማንነታቸው ጋር ብቻ የተገናኘ ሳይሆን  ከፆታዊ ማንነታቸው ጭምር ጋር ነበር።

“ስወለድ ሴት ነበርኩ፤ እንደሴት ግን አይሰማኝም” ይላሉ። “እናም ልጅ እያለሁ በዛ ዕድሜዬ፤ በቃ ወንድ መሆን ነው የምፈልገው ብዬ አስብ ነበር።”

ከሚወዷቸው ማኅበረሰብ የመነጠሉ ስሜት ሥር እየያዘ የመጣው ስለፆታና ስለወሲባዊ ማንነታቸው ያሉትን ዕሴቶች መጠየቅ የጀመሩ ጊዜ ነው።

“እንግዳ ነገር ነው፤ ምክንያቱም ደስ በሚልና ፍቅር ባለው ማኅበረሰብ ውስጥ ነው ‘የነበርሁት’። እናትና አባት ብቻ አልነበረም የነበረኝ፤ ከ10 እስከ 20 የሚደርሱ ወላጆች ነበር የነበሩኝ። እናም የነሱ ሁሉ ልጆች ጭምር” ሚኬሊና የልጅነት ጊዜያቸውን ማኅበረሰብ በፍቅር ያስታውሳሉ።

ከማኅበረሰቡ የመነጠል ስሜት ማዳበር የጀመሩት ዕድሜያቸው ወደ 10 ዓመት ገደማ ሲሆን፤ ማኅበረሰቡ ወንድ እና ሴት እንዴት መሆን አለባቸው ከሚለው ጋር ራሳቸውን ማስተካከል እንዳልቻሉ ማወቅ ሲጀምሩ ነበር።

ሚኬሊና በገጠራማ አርሊንግተን፤ ቴክሳስ መጫወቻ

**“ጉዳዩን የተመለከቱ የቴሌቪዥን ዜናዎች ይወጡ ነበር፤ እናም ቤተሰቦቼ ወይ ዜናውን ያጠፉታል ካልሆነም ደ`ሞ ቻናሉን ይቀይሩታል። እለ አይደል አግባብ አይደለም ብለው በማሰብ።**

**ሚኬሊና**


4411

ሥፍራ ላይ እንዳለ “ቶምቦይ” ከታዛዥ ልጅነት ወደ ጉርምስና እየተሸጋገሩና ስለተማርኳቸው በንቃት ወደማሰብ እየመጡ ነበር።

በዛ ደረጃ እንዲኽ ነው ብለው የሚገልጹበት ቋንቋ ባየኖራቸውም የ“ኩዊር” ግንኙነት የጀመሩት በ13 ዓመታቸው ነበር። ጊዜው እንደ’ተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ ያሉትን የመሠለ ስለ “LGBTQ” ጉዳዮች ጭምር መስማት የጀመሩበት ነበር። በትምህርት ቤት የፈጠሩት ግንኙነት “ኩዊርነትን” እንዴት እንደሚረዱና እንደሚሰይሙ ለማስቻል ወሣኝ የነበረ እንዲሁም በቤታቸው ውስጥ በጉዳዩ ዙሪያ የሚያጋጥማቸውን ተሞክሮ ለማንጸባረቅ የረዳ ነበር።

ጉዳዩን የተመለከቱ የቴሌቭዥን ዜናዎች ይወጡ ነበር፤ እናም ቤተሰቦቼ ወይ ዜናውን ያጠፉታል ካልሆነም ደ’ሞ ቻናሉን ይቀይሩታል። አለ አይደል አግባብ አይደለም ብለው በማሰብ። ልክ አይደለም።” ይላሉ ሚኬሊና። “የፊልም ምሽቶች ነበሩን እና አንድ ፊልም ነበር “Mean Girls” የኩዊር ገጸ⍰ባህሪ የሚታይበት። ቤተሰቦቼ ሄደው ፊልሙን አቋረጡትና አወጡት፤ ያው ልክ አይደለም ብለው በማሰብ።

ሚኬሊና ያሉበት ቦታ ስለወሲባዊ ማንነታቸው የበለጠ ለማወቅ ለሚያደርጉት ጥረት ደጎንነቱ የማያስተማምን እንደሆነ መረዳት ቻሉ። ሁኔታው ከቤተሰቦቻቸው በቻሉት ሁሉ “ኩዊርነታቸውን” እንዲደብቁ ብቻ አልነበረም ያደረጋቸው፤ ወደ መጠጥ፣ ራሳቸውን እንዲጎዱ፣ ድባቴ እንዲሰማቸው እና ሥጉ እንዲሆኑ ጭምር እንጂ። ሁኔታውን ያከፋው ደ’ሞ ማኅበረሰብ ውስጥ የአዕምሮ ጤንነትን የተመለከቱ ድጋፍ የማድረጉና የመረዳቱ ውሥንነት መኖሩ ነበር።

“በቤተሰቤ ታሪክ ውስጥ ከ13 እስከ 20 እድሜ አስቀያሚ ጊዜያት ነበሩ። ስለዛን ጊዜ ምንም ነገር አናወራም ነበር፤ ምክንያቱም ለኔም ሆነ ለቤተሰቦቼ እንዲሁም ለማኅበረሰቡም ጭምር ጥሩ

> **“**
>
> **በዚህ ተሚጋችነት ሂደት ውስጥ ራሴን እንዴት መውደድ እንዳለብኝ መማር ጀመርሁ።**
>
> **ሚኬሊና**

አልነበረም።” ይላሉ ሚኬሊና ያ ትዝታ የሚፈጥርባቸው ስሜት ንግግራቸውን አሁን ድረስ በእንባ እየተናነቀው።

ለኮሌጅ ትምህርት መሄዱ የበለጠ ስለጉዳዩ ለማወቅ ለሚያደርጉት ጥረት ቦታውንና ዐቅሙን በመስጠት ረገድ ትልቅ ትርጉም ያለው ነበር። ምንም እንኳን በሀገሪቱ ካሉት በወግ አጥባቂነቱ ወደር ወደማይገኝለት ተቋም የሄዱ ቢሆንም እና አንዳቸው ለሌላኛቸው የዘር ጥላቻ እንዳላቸው ቢሰማቸውም፤ በዛ ሁሉ መኻል ግን ከቤተሰብ ርቀው እንደመገኘታቸው መጠን ስለራሳቸው የበለጠ ለማወቅ የሚችሉበት ነፃነት የነበረው ቦታ ነበር።

“ከዚህ በኋላ ስሕተት አልነበርኩም፤ ምክንያቱም ማንም ከኔ የተጋነነ ነገር አይጠብቅም” ይላሉ ሚኬሊና። “ማኅበረሰቡ እንደሱ ቢያደርግም፤ ቤተሰብ እና የህበሻ ማኅበረሰብ ሲሆን ግን ይለያል፤ አይደል? ምክንያቱም በቃ በተለየ ሁኔታ ስለሚሰማ።”

ጊዜያዊ ራስን ፍለጋው ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያሉ ባዳበሩት ቋንቋ የሚገለጽ ነበር፤ አሁን ግን ከቤት ርቀው እንደመኖራቸው መጠን ሊተገብሩት፣ በነፃነት ሊያወሩበትና እንደ’ሃሳባቸው ሊኖሩ ይችላሉ። ወደ ስድስት ወር ገደማ እንዳለፈ ሚኬሊና ዩኒቨርስቲው ውስጥ ካሉት የ”LGBTQ” ቡድኖች ጋር ሥራዎችን በማደራጀት መሣተፍ ጀመሩ። አግላይ በሆነ ዩኒቨርስቲ ውስጥ መሆኑ “ነጭ ወንዶች የተወሠነ የሴት ባህሪ በማሳየታቸው እንደ ‘ኩዊር’ ተወስደው የሚመቱበት” በጊቢው ውስጥ የመብት አራማጅ እንዲሆኑ ያደረገና በሕይወታቸው የዘለቀ የመብት አራማጅነት ፍላጎት የፈጠረ ነበር። በርግጥ የሕይወት ተሞክሯቸው “የትውልድ ግንባታና የተገለሉትን ማብቃት ላይ ማዕከሉን ያደረገው” የአሁን ሥራቸው ላይ ተጽዕኖውን አሣርፏል።

ይህ የዩኒቨርስቲ ተሚጋችነት ሌላ ወሣኝ ሚናም ተጫውቷል።

“በዚህ ተሚጋችነት ሂደት ውስጥ ራሴን እንዴት መውደድ እንዳለብኝ መማር ጀመርሁ። ይመስልኛል ማንነት በጊዜያት ውስጥ እንዴት ሊቀየርና ሊፈጠር እንደሚችል ነገሬ ማለት ጠቃሚ ነው።” ይላሉ። “ራሴን የመውደዱን ሂደት ጀመርሁ እናም ከቤተሰቤና ከማኅበረሰቡ የወረስኩትን ውስጤ የሰረጸውን የራስ ጥላቻ ከውስጤ ፍጹም ማስወገድ ላይ መሥራት ጀመርሁ።

ቤተሰቦቻቸውና ማኅበረሰቡ ሆን ብሎ እነሱን ለመጉዳት ፈልጎ እንዳልሆነ መረዳቱ ቢኖርም፤ የቀደመውን አስተምኽሮ ማረም የሚያስችል አስፈላጊው ነገር እና ማንነት ተቀያያሪ ነገር እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

ሚኬሊና በዩኒቨርስቲው ውስጥ ጠንካራና የማይናቅ “ኩዊርነታቸውን” ግልጽ ያደረጉ ሰው ነበሩ፤ በቤት ውስጥ ግን ማንነታቸውን አልተናገሩም ዝምታን መምረጣቸው ከባድ ነበር። በቤት ውስጥ ያላቸውን ዝምታ ዩኒቨርስቲ ላይ ካላቸው ግልጽነት ጋር ማስታረቅ ግን አልቻሉም፤ እናም ደ’ሞ በመጨረሻም ያንን ነፃነት ቤት ውስጥ ለማወጅ ጊዜው እንደሆነ ተሰማቸው።

ከመነሻውም ከቤተሰቦቻቸው

ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዳይቋረጥና የሚልኩላቸውንም ገንዘብ እንዳያቆሙባቸው በማሰብ ኮሌጅ እስኪጨርሱ ለመታገስ ዐቅደው ነበር። በዛ መረዳት የቤተሰቦቻቸው ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል ሙሉ በሙሉ ርግጠኛ አልነበሩም። ያም ሆኖ ግን የሆነ ጊዜ ላይ ከዚህ በላይ ሊዋሹ እንደማይችሉ ተረዱ እናም ለራስና ለሌሎች ማንነትን በልኩ መግለጽ የሚሰማውን ስሜት መለማመድን ከጀመሩ በኋላ ገሸሽ ማለቱ ከባድ ነበር።

ስለዚኽ ለሙከራ ያኽል ለወንድማቸው ስለወሲባዊ ማንነታቸው ነገሩት እናም በአውንታዊ ምላሹ ተበረታቱ። በማስከተልም በጣም ለሚቀርቧት አክስታቸው ነገሯት፤ አክስታቸውም በሚቻለው ፍጥነት ለእናታቸው እንዲነግሯቸው ጎተጎቷቸው።

በአክስትየው ጉትጎታ መሠረት የቤተሰብ ሽርሽር በሄዱበት እግራቸውን ለማፍታታት በሚራበዱበት ጊዜ ለእናታቸው ነገሯት። የእናታቸው ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ነበሩ።

“ትመታኛለች ብዬ አስቤ ነበር፣ ትገፈትረኛለች ብዬም አሰብኩ። ምን ሊፈጠር እንደሚችል ዐላውቅም ግን እይተገፋፋሁ ነበር። ለሚመጣው ሁሉ ራሴን ማዘጋጀቴን ግን አስታወሳለሁ። እናም ያልኳትን መቼም አልረሳውም ‘ጌ ነኝ’፤ እናም ምን አልደነቀትም፤ ዕርምጃዋን እንኳን አልገታችም፤ አልቆመችም፤ በእግራችን መንሸራሸራችንን ቀጠልን” ሚኬሊና ያስታውሳሉ።

ከትንሽ ማሰብ በኋላ እናታቸው ጠየቀች “ምንድን ነው እንደዛ እንድትዪ ያደረገሽ?” የመጀመሪያው ጥያቄ በሌሎች ተከታታይ ጥያቄዎች ታጀበ። እንዴት ዐወቅሽ? መች ነው ያወቅሽው? ከድሮውም ታውቂው ነበር? ለምን ይኽን መረጥሽ ምክንያቱም ከባድ ሕይወት ነው? እነዛ የመነሻ ጥያቄዎች እናታቸው

“

**እናም [እናቴን] ያልኳትን መቼም አልረሳውም ‘ጌ ነኝ’፤ እናም ምን አልደነቀትም፤ ዕርምጃዋን እንኳን አልገታችም፤ አልቆመችም፤ በእግራችን መንሸራሸራችንን ቀጠልን”**

**ሚኬሊና**



“ጨርሶ ምንም አልገባኝም” ወደሚል ጥያቄ እንድታመራ አደረጋት።

ሚኬሊና የተሻለ ባሉት መንገድ ለመግለጽ እንደሞከሩ ይናገራሉ። ይህ የምርጫ ጉዳይ እንዳልሆነና ሁሌም እንዲህ እንደነበሩ እናም ራሳቸውን መረዳት የጀመሩትና መግለጽ የቻሉት አሁን እንደሆነ አስረዱ።

ይኽ ነበር ሚኬሊና እና እናታቸውን በጉዟቸው ላይ አንድ ላይ ያስቀመጣቸው ንግግር፤ ይኽ ንግግራቸው በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ተግባቡት ልዩ አደረገው። እናታቸው ሚኬሊና “ያሳደጓት ሴት ልጃቸው እስከሆነች ድረስ” ከሚኬሊና ማንነት ጋር ራሳቸውን ማስማማት ቻሉ።

ሊቀየር የሚችለው ነገር ማንን እንደምታገቢ እጠብቅ የነበረው ብቻ ከሆነ እግር የለም።እሱ ያስማማናል።” ሚኬሊና እናቷ ያለቻትን ታስታውሳለች። “ቋንቋ አጠቃቀሟን እያስተካከልኩላት ነው፤ ነገር ግን መገለጫው ያ ነው።”

ከዛ በኋላ እናታቸው የሚኬሊናን አባት ለማናገርና ስለሚኬሊና ማንነት በተመለከተ ከሐበሻ ማኅበረሰብ ጋር ወሬ ከተነሣ ለመጋፈጥ ፍቃደኛ ሆነች።

“ከሐበሻ ማኅበረሰብ ጋር እንደመገናኘቱ መጠን የተወሠነ ነገር ማውራት ነበረብኝ፤ እናም ውጤቱን ሰዎቸ ምን እንደተሰማቸው ማወቅ አልቻልኩም፤ ነገር ግን ዛሬ ላይ ባሳደጉኝ ሁሉ የተወደድኩ እንደሆንኩ፣ እንደታቀፍኩና እንደተቀበሉኝ መናገር እችላለሁ። ቤት ሄጄ ፍቅረኛዬን ለሻይ ቡና መውሰድ እችላለሁ።” ይላሉ ሚኬሊና

ለሚኬሊና የፆታዊ ማንነትም በተመሳሳይ መልኩ ወሣኝ ጉዳይ ነበር። ምንም እንኳን መነሻቸው ላይ ራሳቸውን እንደ “ባዮሴክሹዋል” በማስከተልም “ሌዝቢያን” ቆጥረው የነበረ ቢሆንም፤ “ሴት” ትክክለኛ ስርዐተ ፆታቸውን እንደማይገልጹ ያውቁታል። እንደ ልጅ፤ ከልጅም የስድስት ዓመት ልጅ ልክ

“እንደ ሴት አይሰማኝም ነበር” ይላሉ። ጥያቄዎቻቸው ለሴት ባላቸው ተማርኮ መልስ እንዳገኙ ወይም እንደተፈቱ ይሰማቸው ስለነበር ከመነሻው ስለስርዐተ ፆታዊ ጥያቄዎቻቸው መልስ ለማግኘት አልሞከሩም። ሚኬሊና “ለሴት ተማርኮ አለኝ፤ ለዛም ይመስለኛል ወንድ ለመሆን ያሰብኩት ለዛ ነበር” ብለው ያስቡ ነበር።

በመጨረሻም ከ“ኩዊር” ማኅበረሰብ ጋር ያላቸው ማኅበር ነበር ስለስርዐተ ፆታዊ ማንነታቸው ለማወቅ ጥረት እንዲያደርጉ የገፋፋቸው። የሚኬሊና “ኩዊር” ማኅበረሰብ እና ትምህርት እየሰፋ ሄደ፤ ስለ“ኩዊር” የሚያጠና ክፍለ-ጊዜዎችን ይከታተሉ ነበር፤ ሽግግር ላይ ካሉ “ትራንስጀንደር” ሰዎች ጋርም ነበሩ።

“ከነሱ ጋር በሽግግር ሂደት ውስጥ ዕያለፍኩ ነበር ወይም እነሱ በ’ንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሲያልፉ ዐይቻለሁ። በዚያን ጊዜ እንዲህ ‘ተመስገን፤ ኃሌሉያ፤ ይኸው ነው ቢቃ፤ እኔ ጀብራራ አይደለሁም፤ በመሠረቱ ይኽ የኔ እውነታ ነው፥ አውራቦቱም አለ።’ ማለቴን አስታውሳለሁ” ይላልሉ ሚኬሊና ‘ስርዐተ ፆታ’፣ ‘ኩዊር’፣ ‘ነን󠄀ባይነሪ’ የሚለው ቋንቋው ሲገባኝ የራሱ ተፅዕኖ ነበረው፥ በደንብ ማንነቴን ገልፀልኝ።”

ለሚኬሊና እና ለቤተሰቢ ጉዞው ቀጥላል። ከቤተሰቦቻቸው ጋር ስርዐተ ፆታዊ ጉዳዮችን የተመለከቱ ገና ሰፋ ያሉ ውይይቶች ይጠብቃቸዋል።

“ይመስለኛል ‘ኩዊር ማንነቴ’ የተገለጸው እያደኩ ስመጣ ነው፤ ምክንያቱም ራስሽን እንዴት በጥልቅ መውደድ እንዳለብሽ እየተማርሽ ትመጫለሽ። ልክ ቤተሰቦቼንና ማኅበረሰቤን ያለገደብ እነሱነታቸውን መውደድ እንዳለብኝ እንደተማርሁት ሁሉ ማለት ነው።” ይላሉ ሚኬሊና። “እንዳንዴ እነዚህ ነገሮች ቅራኔ ውስጥ እንዳሉ ይሰማል፤ ያም ሆኖ እንዳችን ለሌላኛችን ትንሽ ክፍተት መተው እንችላለን፤ ሳይገባን ወይም ሳንግባባ የቀረን ቢሆንም እንኳን።”

> “
>
> **ይመስለኛል ‘ኩዊር ማንነቴ’ እየተሻሻለ የመጣው እያደኩ ስመጣ ነው፤ ምክንያቱም ራስሽን እንዴት በጥልቅ መውደድ እንዳለብሽ እየተማርሽ ትመጫለሽ።**
>
> ሚኬሊና

# ዮርዳኖስ

> “
> **አስተማማኝ መስሎ ሲሰማኝ፤ በአካል በጭራሽ ባልሞከረውም “በኦንላየን” ግን ለሰዎች ወሲባዊ ማንነቴን ግልጽ አድርጌ ዐውቃለሁ። በጠባብ የክልል ርዕሰ - ከተማ አንዷ’ መኖሬም መጠን ወሲባዊ ማንነቴን ግልጽ ለማድረግ ደኅንነት አይሰማኝም።**
>
> ዮርዳኖስ

ከአንዲት ሴት ፍቅር እንደያዛት ማወቋ ነበር በመጨረሻው ወሲባዊ ማንነቷን ላፈቀረቻት ልጅ ይፋ ለማድርግ የነበራትን ውሣኔ ያጠናከረው። በኢትዮጵያ የክልል መቀመጫ በሆነች ከተማ የምትኖረው “ወንዳ’ወንዳዊ” ባህሪ ያላት ዮርዳኖስ 14 ወይም 15 ዓመት አካባቢ ቢሆናት ነበር በሰዓቱ።

“ልደብቀው እንኳን እስከማልችል ድርስ በፍቅሯ ከንፌ ነበር” ዮርዳኖስ ስታስታውስ። “ከጓደኞቼ አንዷ እንኳን አልነበረችም፤ በቅጡም አላውቃት።”

ዮርዳኖስ ሁሌም ቢሆን ከዕድሜ ዕኩዮቿ የተለየች እንደሆነች ታውቀው ነበር። ነገር ግን ስለሷ የተለየው ነገር ምን እንደሆነ የምትገልጽበት የቋንቋው መረዳቱ ወይም ልዩነቱን እንዴት እንደምትሰይምው አታውቅም ነበር። በአካባቢዋ የሚሰማትን ስሜት ትርጉም ሊያስገኝላት የሚችል ነገር



አልነበረም።

ለልጅቷ በፍቅር ከወደቀች በኋላ እንኳን ብዙ ዐቅሟን ስሜቷን በመካድ እና ከራሷ ጋር ቅራኔዎችን በማስተናገድ አጥፍታለች። ምንም ያኽል ለሌሎች ሴቶች የሚሰማትን ተማርኮ ልታስቆመው ብትሞክርም፤ ሊሳካላት አለመቻሉ ነው የሚሰማትን ስሜት የምታስተናግድበት መንገድ መፈለግ እንዳለባት የወሠነችው።

“ምን እንደሚሰማኝ ለማወቅ ረጅም ጊዜ ወስዶብኛል፤ ነገር ግን ከተወሠነ ዕድሜ በኋላ፤ መቀበል ነበረብኝ” ትላለች ዮርዳኖስ።

ዮርዳኖስ ላይ ቅሬታ የፈጠረባት ተማርኮዋና የሚሰማትን ስሜት ቤተሰቦቿና በማኅበረሰቡ እንደ ዓለም ዐቀፍ እውነት ከሚቆጠረው አስተሳሰብ ጋር ለማስማማት ስትሞክር ነው። ኃይማኖተኛ ቤተሰቦቿ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነትን የኃጢያቶች ሁሉ የበላይና ከኃይማኖተኛነት ማፈንገጥ አድርገው ነበር የሚወስዱት። ዮርዳኖስም ይኽን አመለካከት ከልቧ ትውስደው ስለነበር የራሷን መንገድ ለመቀየስ ከባድ ሆነባት።


በመጨረሻም ወሲባዊ ተማርኮዋን እና ዕምነቷን በማስታረቅ መቀበል ቻለች። ተማርኮዋንና ስሜቷን ልትቆጣጠር እንደማትችል ገብቷት ነበር። ለሌላ ሴቶች ያላት መሳብ የማንነቷ መገለጫ “የተፈጥሮዋ” አንዱ አካል እንደሆነ መረዳት ችላለች። ምንም ያኽል ለነገሩ የነበራት መረዳት ዘገምተኛ የነበረ ቢሆንም ሌላ ሴቶችን መውደድ ኃጢያት ነው ከሚለው ኃይማኖታዊ አስተምህሮ ነፃ የሚያደርግ ነበር።

“ስህተት አልሠራሁም፤ ስሜቴ ስለፍቅር ነው፤ ያ ደ’ሞ ተፈጥሯዊ ነው። ስሜቱን እኔ ስለፈለኩት አልነበረም፣ ሌሎች ሰዎች እንደሚያስቡትም በሌላ ሰው ተፅዕኖ ውስጥ ወድቄም አይደለም፣ ጭንቅላቴ ስለተመረዘ ወይም ፊልም የማየቴ ውጤትም አልነበረም” ትላለች ዮርዳኖስ። “የሚሰማኝ እንደዚኽ ነው እና ደ’ሞ ይኽ አዲስ ነው ልል አልችልም። ሁሌም እንዲኽ እንደነበርኩ ዐውቃለሁ። ለሌሎች ልዋሽ እችላለሁ፤ ነገር ግን ዕውነቱን ዐውቀዋለሁ።”

ሌዝቢያን የመሆኗ ግልጽ መረዳቱ ቢኖራትም፤ በጊዜው ዮርዳኖስ ማንነቷን ወደ “ኖርማል” መቀየር እንደምትችል ታምን ስለነበር፤ በትጋት

**ይኽን ማኅበረሰብ ካገኘሁ በኋላ ራሴን ሙሉ በሙሉ ወደ መቀበል መጣሁ። ብዙ ሰዎች ራሳቸውን ሲቀበሉ በማየት ምቾት አግኝቼ ነበር።**

ዮርዳኖስ



ሌዝቢያንነቷን መካድ የሚያስችሏትን መንገዶች ሁሉ ትፈልግ ነበር። ምንም እንኳን ሌዝቢያን እንደሆነች ብታውቅም፤ ስህተት ነው ብላ ስለምታስብ በኃይል ተጭና ለመቀየር ጥረት ታደርግ ነበር።

ራሷን እንድትቀበል የሚያደርጋት አጋጣሚ የተፈጠረው ወደ 19 ዓመቷ ስትሸጋገር ነበር። ራሷን ለመቀበሏ እንደ አንድ ምክንያት የሚጠቀሰው ከሌሎች የኢትዮጵያ "LGBTQ+" ማኅበረሰብ ጋር ግንኙነት መፍጠር መቻሏ ነበር። "ፌስቡክ" እና ሌሎች ማኅበራዊ ትሥሥር ገጾች ላይ "ኩዊር" የሆኑ ሰዎችን በመፈለግ እዛ ላይ በሚጋሩ አንዳንድ ጽሑፎች ተደነቀች። ከሌሎች "ኩዊር" ሰዎች ጋር መጻጻፍ ጀመራ የተፈጠረው ተግባቦት ከጠበቀችው በላይ ነበር የሆነባት።

"ይኽን ማኅበረሰብ ካገኘሁ በኋላ ራሴን ሙሉ በሙሉ ወደ መቀበል መጣሁ። ብዙ ሰዎች ራሳቸውን ሲቀበሉ በማየት ምቾት አግኝቼ ነበር።" ትላለች። "ይኽ ምንም ማለት እንዳልሆነ ዐወኩ እናም እንደትልቅ ነገር ሊታይ ስለማይገባው ስለጉዳዩ መጨነቄን አቆምኩኝ።"

መጀመሪያ ወሲባዊ ማንነቷን ግልጽ ያደረገችላት፤ ከሷ ጋር እንዲህ ነው ተብሎ ያልተነገረለት፣ ያልተገለጸና ትርጉም ያልተሰጠው ግንኙነት ለነበራት ልጅ ነበር። ምንም እንኳን አካላዊ መቀራረብ ያለበት ግንኙነት ውስጥ ገብተው የነበረ ቢሆንም አውርተውበት ግን ዐያውቁም። ዮርዳኖስ ይኽ ዝምታቸው ትንፋሽ የሚያሳጣት ሲሆንባት በግልጽ ለግንኙነታቸው ስም መስጠት እንድምትፍልግና ያላቸው ግንኙነት የፍቅር እንድሆነ ጎተጎተች።

ሌላኛዋ ልጅ ግን ግንኙነታቸው የተሳለበትን መንገድ በጽኑ እንደምትቃወምና "ሌዝቢያን" እንዳልሆነች፤ ያላት ተማርኮም ለዮርዳኖስ ብቻ እንደሆነ፤ እሱም ቢሆን ከሚጋሩት አካላዊ መቀራረቡ በላይ የጓደኝነት እንድሆነ ተናገረች። ዮርዳኖስ ግን ይኽ

“

**ስህተት አልሠራሁም፤ ስሜቴ ስለፍቅር ነው፤ ያ ደ' ሞ ተፈጥሯዊ ነው።... ሁሌም እንዲኽ እንደነበርኩ ዐውቃለሁ። ከሌሎች ልዋሽ እችላለሁ፤ ነገር ግን ሰውነቱን ዐውቀዋለሁ።**

**ዮርዳኖስ**

ለሷ የማንነት ጉዳይ እንደሆነና የሷ "ሌዝቢያንነት" መሳለቂያ እንደሆነ እናም ተቀባይነት እንዳጣ ገለጸች።

"ለምንድን ነው ይኽን ታሪክ ያመጣሽው? እንዴት ይኽን ልትይ ቻልሽ? እወድሻለሁ ግን እኔ እንደዛ አይደለሁም" ዮርዳኖስ በመጨረሻም እንዴት እንደሚሰማት ለልጅቷ ለመናገር ብርታቱን ስታገኝ የልጅቷ ቃላቶች ምን እንደነበሩ ታስታውሳለች።

ዮርዳኖስ በማስከተልም ለልጅቷ ያላት ፍቅር ሊቆም ስላልቻለ እና ለመጀመሪያ ፍቅሯ ዕድል ልትሰጠው ስለፈለገች "በቴክስት" ስለወሲባዊ ማንነቷ ግልጽ ልትሆንላት ወሠነች። በመጨረሻም ዮርዳኖስ "ሌዝቢያን" መሆኗን ከነገረቻት በኋላ ጓደኝነታቸውን እንዲያቆሙ ሃሳብ አቀረበች። ልጅቷም እሷም ለዮርዳኖስ ስሜት እንዳላት ነገር ግን በጉዳዩ ላይ ምንም ማድረግ እንደሚቸግራት ነገረቻት። በሰይጣን እየተፈተኑ እንደሆነና ለዛ ስሜት መገዛት እንደሌለባቸውም አስረዳቻት።

ከዛን ጊዜ በኋላ ዮርዳኖስ የ"LGBTQ+" ማኅበረሰብ አባል መሆኑን 'ርግጠኛ እስካልሆነች ድረስ ወይም ለ"LGBTQ+" ማኅበረሰብ ድጋፍ እንዳለው ካልተማመነች በስተቀር ወሲባዊ ማንነቷን ለማንም ሰው ግልጽ ማድረግ እንደሌለባት ተማረች። ምንም እንኳን ቤተሰቦቿ ውስጥ ላሉ ሰዎች ወሲባዊ ማንነቷን ጨርሶ ነግራቸው ባታውቅም እንደሚያውቁ ግን ትገምታለች።

"አስተማማኝ መስሎ ሲሰማኝ፤ በአካል በጭራሽ ባልሞከረውም "በኦንላየን" ግን ለሰዎች ወሲባዊ ማንነቴን ግልጽ አድርጌ ዐውቃለሁ። በጠባብ የክልል ርዕሰ-ከተማ እንደ'መኖሬም መጠን ወሲባዊ ማንነቴን ግልጽ ለማድረግ ደኅንነት አይሰማኝም" ትላለች ዮርዳኖስ። "ኢትዮጵያ ውስጥ ለምንኖር 'ኩዊሮች' ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድርግ ከባድ አደጋ የሚያጠላ ኃላፊነት መውሰድ ነው፤ እናም የሚመከር አይደለም።"

# ብሌን

“ወሲባዊ ማንነቴን ለአባቴ ግልጽ አደረኩለት እናም ምላሹ ከምንም በላይ ተስፋ ላደርገው የምችለው ነገር ነበር ምክንያቱ አባቴ በሚደንቅ ሁኔታ ተረድቶኝ ነበር። ፊልም ላይ ለቤተሰቦቻቸው ስለወሲባዊ ማንነታቸው ግልጽ ሲያደርጉ ቤተሰቦቻቸው የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ ነበር ያደረገው፤ አለ አይደል “አውቃለሁ፤ እወድሻለሁ፤ የሆንሽውን መሆን ትችያለሽ” ብሌን ከበደ ስለወሲባዊ ማንነቷ ለአባቷ ግልጽ ያደረገችበትን አጋጣሚ በፍቅር ታስታውሰዋለች።

ብሌን “ጀንደር ኲዊር” ወይም “ጀንደር ነን ኮንፈርሚንግ”  አሜሪካ ያደገች ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነች። (አጠራር፥ እሷ/እሳቸው)

ብሌን ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድረግን እንደ ጉዞ ነው የምትቆጥረው። ከልጅነታቸው ጀምሮ የተለዩ እንደሆኑ ያውቁት ነበር፤ ነገር ግን በአብዛኛው ነጮች በሆኑበት ተቋም ውስጥ እንደመማራቸው መጠን የሚሰማቸውን ልዩነት ደብቀው ከፍላጎታቸው ውጪ ወንድ “ዴት” አድርገዋል።

በመፈለግ ውስጥ ያለውን ተግዳሮት ስትገልጽ “በየቀኑ ስለራስሽ የተወሠነ ማወቅ ነው።” ትላለች ብሌን። “የራሳቸውን የሆነ የተሻለ የኲዊር ሕይወት የሚኖሩ ሌሎች ኲዊር ሰዎች ዐይቼ አላውቅም። ብዙ ሰዎች ኲዊር መሆንና



*ብሌን ከበደ ከአባታቸው ጋር*

“

ወሲባዊ ማንነቴን ለአባቴ ግልጽ አደረኩለት እናም ምላሹ ከምንም በላይ ተስፋ ላደርገው የምችለው ነገር ነበር ምክንያቱ አባቴ በሚደንቅ ሁኔታ ተረድቶኝ ነበር።

ብሌን



ኢትዮጵያዊ መሆን ሁለት የተነጣጠሉ ነገሮች ናቸው ይላሉ።"

ወሲባዊ ማንነታቸውን ግልጽ ሲያደርጉ፤ መጀመሪያ እንደ "ባይሴክሹዋል"፣ ከዛ እንደ "ሌዝቢያን"፣ በስተመጨረሻም እንደ "ኲዊር" ነበር። በዛ ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ በማድረግና ራስን በመፈለግ ውስጥ የረዳቸው ነገር ቢኖር "ኦንላየን" ላይ ከኢትዮጵያ የ"LGBTQ+" ማኅበረሰብ ጋር መገናኘት መቻል ነበር።

"ኦንላየን" ላይ የተወሡ "ኲዊር" ኢትዮጵያውያንን አገኙ እናም "በቨርቹዋል" ኢ-መደበኛ ስብሰባ ከ"ኲዊር" ኢትዮጵያውያን ጋር መተዋወቅ ጀመሩ። ከተሰብሳቢዎቹ ውስጥ አውሮፓ ያሉ ኲዊሮች፣ አሜሪካ ያሉ ኲዊሮች እንዲሁም አንድ ሰው ከአዲስ አበባ ጭምር ተሳትፈውበታል። ይህውም የበለጠ አደጋ ያላቸውን ኃላፊነቶች ለመውሰድ ተነሣሽነት ለመፍጠር ረድቷቸዋል።

"ወሲባዊ ማንነቴን የበለጠ ለመግለጽ እንድሞክር ጊዜው የደረሰ መሰለኝ፤ በሁኔታው በጣም ነበር የተበረታታሁት፤ ምክንያቱም አሁን ይኽ ሁሉ ጦረኛ አብሮኝ እንዳለ ተሰምቶኛል፤ ይህ ሁሉ ጦር ከጀርባዬ አለ። አሁን እኔ ብቻ አይደለሁም ማለት እችላለሁ፤ እናም ይኽ ሁሉ ሰው እንደኔ ሆኖ ሳለ እንዴት ላትቀበሉኝ ትችላላቹ?" ትላለች ብሌን።

ከዛ በኃላ ወርሃዊው የ"ቨርቹዋል" ኢ-መደበኛ የኲዊሮች ስብሰባ በመላው አሜሪካ በአካል ወደሚደረግ ኢ-መደበኛ ስብሰባ ተሸጋገረ። በርግጥ በቅርቡ አሁን ላይ ከደባሎቻቸው ጋር በሚጋሩት ቤት ለ"LGBTQ+" ኢትዮጵያዊያን የ"ሃሎዊን" ድግስ አዘጋጅታ ነበር፤ "ኲዊር" ኢትዮጵያዊያን ለሆኑትና በመጀመሪያው ኢ-መደበኛ "ቨርቹዋል" ስብሰባ ላይ ላገኟቸው ወዳጆች።

ራሳቸውን መቀበላቸው ሴትን "ዴት" ወደ'ማድረግ አመራ፤ እናም ኮሌጅ እያሉ "ዴት" ከሚያደርጓቸው ሴቶች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ወደፍቅር

> **ወሲባዊ ማንነታችንን ግልጽ ስናደርግ የተዋሃደን "ሆሞፎቢያ" እና "ትራንስፎቢያ" ላይ እንደምንሠራ ሁሉ፤ ወላጆቻችንም ያን ዓይነት ሕክምና ማድረግ አለባቸው።**
>
> ብሌን

አጣማሪነት የሚያድግ ስለነበር ነው ለእናቶቻቸው ወሲባዊ ማንነታቸውን ግልጽ ለማድረግ እንዲፈልጉ አደረጋቸው። ቤላይን ከእናቶቻቸው ጋር ጥሩ ቀረቤታ ነበራት፤ እናም ይህ ቀረቤታ ፈጣን ተቀባይነት ያስገኝልናል ብለው አሰቡ።

ከስሜታዊነቷ መለስ ካለች በኋላ፤ ብሌን "በጣም አዝናለሁ ስለዚህ ነገር ሳወራ ስሜታዊ እሆናለሁ" ብላ ከተናገረች በኋላ ትንሽ ትንፋሽ መውሰድ ነበረባት ንግግሯን ለመቀጠል።

"ለእናቴ ስለወሲባዊ ማንነቴ ግልጽ አደረኩላት፤ አጋጣሚው በጣም አስቀያሚ ነበር። የምትቀበለኝ አልነበረችም። ለሳምንታት አላወራችኝም እናም በጣም ልብ የሚሰብር ነገር ነበር፤ ምክንያቱም በጣም እንቀራረብ ነበርና።" ትላለች።

እናቷ በዙሪያቸው ያለው ማኅበረሰብ ምን ይላል የሚለው ያስጨንቃቸው ነበር፤ እናም ብሌን በዛ ሁኔታ ውስጥ ለትንሽ ጊዜ እያለፈች እንደሆነ ርግጠኛ ነበሩ። ብሌን እናቷ አብዛኛውን ዕድሜዋን አሜሪካ እንደመኖሯ፣ አሜሪካ ባህል ውስጥ እንዳለፈና ብዙም ኃይማኖተኛ እንዳለመሆኗ መጠን ትቀበለኛለች የሚል ዕምነት ስለነበራት በጣም ተበሳጨች። የእናቷ እሷን አለመቀበል (በአሳማኝ ምክንያት ሣይሆን እንዲሁ ትክሻዋ ስላልፈቀደ) በኢትዮጵያ ባህል ውስጥ ምን ያኽል ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት ሥር የሠደደ እንደሆነ ትምህርት ሰጥቷታል።

የእናቷ ምላሽ "በሥጋ የማይዛመዷትን ቤተሰብ" (LGBTQ+ ኢትዮጵያውያን) የመፈለግ እና ራሳቸውን መደበቅ ከማይጠበቅባቸው ሰዎች አጋርነትን የመቀበል ቁርጠኛነቷን አጠናከረላት።

"ሁሉም ኲዊር ኢትዮጵያውያን 'እኔ ብቸኛዋ ነኝ' እና 'እዚህ ዓለም ላይ ለብቻዬ ነው ያለሁት' እንደሚሉ ይሰማኛል። ስለዚህም ጊዜ ወስጄ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ሄድኩኝ። ብዙ

እንዳለን ዐውቃለሁ ምክንያቱም ሌላ ሰውም መኖር አለበት። እናም አንላየን ማደራጀት ጀመርሁኝ” ትላለች ብሌን።

ለሷ፤ ከሌሎች ኲዊር ኢትዮጵያውያን እና ኤርትራዊያን “በሥጋ ከማይዛመዷቸው ቤተሰቦች” ጋር በመሆኑ የሚያገኙት ኃይል ሕይወት ቀያሪ ነበር የሆነው።

“አንድ ላይ ስንሆን [ኲዊር አትዮጵያውያን] በጣም ከባድ ነው። ብዙ ዓይነት ሰቆቃዎችን ተሸክመናል። ምናልባትም ወሲባዊ ማንነታችንን ግልጽ ለማድረግ ሞክረን በቤተሰቦቻችን ተትተናል ወይም ድ`ሞ ቤተሰቦቻችን ራሳችንን ግልጽ ስላወጣን ከዚህ በኋላ አያወሩንም።” ይላሉ። “በተመሳሳይ መንገድ ላይ መሆናችንና ማኅበረሰብ መሆናችን የመንፈስ ጥንካሬ ብቻ አይደለም የሚሰጠው ብቻሽን እንዳልሆንሽና ብቸኛ እንዳልሆንሽ ማወቁ የሚሰጠው ሕክምና ጭምር እንጂ።”

> “
>
> **አንድ ላይ ስንሆን [ኲዊር አትዮጵያውያን] በጣም ከባድ ነው። ብዙ ዓይነት ሰቆቃዎችን ተሸክመናል። ምናልባትም ወሲባዊ ማንነታችንን ግልጽ ለማድረግ ሞክረን በቤተሰቦቻችን ተትተናል ወይም ደ`ሞ ቤተሰቦቻችን ራሳችንን ግልጽ ስላወጣን ከዚህ በኋላ አያወሩንም።**
>
> ብሌን

ከሁሉም የተለየ የነበረው አባቷ ነው። ዋና ተባባሪያቸው የነበረው እሱ ነው እናም ስለኲዊር ባህል፣ ቋንቋቸውንና የሚመለከቱትን ፊልም የማወቅ ከፍ ያለ ፍላጎት ነበረው። ተሚጋች እስከመሆን ድረስ ለሷ ብቻ ሣይሆን ለሌሎች ኲዊሮችና ቤተሰቦቻቸው ጭምር። ከሌሎች ኲዊር ወላጆች ጋር በቀላሉ የመነጋገርና የመስማት ችሎታውን ተጠቅሞ በኲዊሮችና በቤተሰቦቻቸው መካከል ያለውን የትውልድ ክፍተት ለመሙላት እንደድልድይ መሣሪያ ሆኗል። ትላልቅ ሰዎች ከዕድሜ አቻዎቻቸው ጋር በተሻለ ራሳቸውን ስለሚያመሳስሉ ለኲዊሮች ለቤተሰቦቻቸው ግልጽ የመውጣቱን ነገር ቀላል አድርጎላቸው ነበር።

“የኛና የቀደሙት ትውልዶች ላይ መሠራት ያለበት ብዙ ሕክምና አለ።” ትላለች ብሌን። “ወሲባዊ ማንነታችንን ግልጽ ስናደርግ የተዋሃደን “ሆሞፎቢያ” እና “ትራንስፎቢያ” ላይ እንደምንሠራ ሁሉ፤ ወላጆቻችንም ያን ዓይነት ሕክምና ማድረግ አለባቸው።”



“

**ምንም ያክል በሕዝባችንና በባህላችን የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት ቢደርስብንም በኢትዮጵያዊነታችን የኩራት ስሜት አለን።**

ብሌን

ለብሌን ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድረግ ልክ እንደ ጉዞ ነው፤ ያ ጉዞ የስርዐተ ፆታ ማንነትን ፈለጎ ማግኘትን ይጨምራል።

“እኔ ስርዐተ ፆታዬን ወንድ ወይንም ሴት ብዬ አላስቀምጠውም ‘ጀንደር ኩዊር’ ወይም ‘ጀንደር ነን ኮንፎርሚንግ’ ይገልፀኛል ፤ ምክንያቱም እኔ የአንድን ሰው ስርዐተ ፆታ ወንድ ወይም ደ`ሞ ሴት ብሎ በመበየን አላምንም። እኔ በመካከል ስላለው ክፍተት ወይም ወንድና ሴት ከሚለው የሚሻገር ብዙ ሊባልለት የሚችል ነገር አለ ብዬ አስባለሁ።” ትላለች።

የስርዐተ ፆታ ማንነትን ግልጽ ማድረግ በኩዊር ማኅበረሰብ ውስጥ ሳይቀር ተቃውሞ ይገጥመዋል። ‘ጀንደር ባይናሪ’ አንድን ሰው ወንድ ወይም ሴት ብሎ የሚለያይበት ሥርዓት- በኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ውስጥ  ሰዎች ራሳቸውን ትክክል ነው ባሉት መንገድ እንዳይሰይሙ ባለመፍቅድ ትልቅ ሚና አለው። ይህ “ትራንስፎቢያ” በ“LGBTQ+” ማኅበረሰብ ውስጥ አለ ፤ ይህውም ራሳቸውን ወንድ ወይም ሴት ብሎ ከሚሰይመው ሥርዓት ውጪ የሚያገኙትን ያከብድባቸዋል።

“ሁላችን በመፈለግ መንገድ ላይ ነን እና እየተማርን ነው፤ አንዳንድ ሰዎች ግን እስካሁንም እዛም አልደረሱም። እናም በማኅበሰባችን ውስጥ እንደዛ ዓይነት ትምህርት መፈጠር ቢቻል ቆንጆ ነው፤ ይመስለኛል ያ ነው የጎደለን ነገር።” ይላሉ።

ብሌን “ማንነትን ግልጽ ማድረግ መቼም የማያበቃ ሂደት ነው። ከሁሉም በላይ ወሣኙ ነገር ለራሳችን ስለጉዳዩ ግልጽ መሆን መቻል ነው። ኢትዮጵያውያን “LGBTQ+” ሰዎች ሥር የሠደደ “ሆሞፎቢያ” እና “ትራንስፎቢያ” ተጋርጦባቸዋል። ትልቁ ኃቅ ኩዊር ኢትዮጵያዊያን በተደጋጋሚ ይኽ ነገር ስህተት ነው፤ ኩዊር መሆኑ ‘በምዕራቡ ዓለም ባህል የመወረስ’ ውጤት ነው እየተባሉ እየተነገራቸው ጭምር ከራሳቸው ጋር ሰላም መፍጠር መቻልና ራሳቸውን መፈለግ መቻላቸው እጅግ ድንቅ ነው።” ትላለች።

ብሌን አንድ ሃሳባዊ ጥያቄ ታነሣለች። ራስን ከኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ጋር ለማስተካከል ሲባል በቀላሉ ከኩዊርነት ማምለጥ ይቻላል ወይም ደ’ሞ መደበቅ? መልሱ እንደጥያቄው ቀላል ሆኖ ነበር ያገኘችው።

“አንዳንዴ እንደዛ ያለ ስሜት ይሰማል፤ ግን አንፈቅድለትም። ባይሆን ወደ ነገሩ በጥልቅ በመግባት እኛ ኩዊርና ኢትዮጵያዊ መሆናችንን በደንብ ግልጽ አደረግን። ጉዳዩ ልንሸሽው የምንሞክረው አንዳች ነገር አይደለም።” ይላሉ። “ምንም ያኽል በሕዝባችንና በባህላችን የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ጠልነት ቢደርስብንም በኢትዮጵያዊነታችን የኩራት ስሜት አለን።”



# ራስን መግለጥ፦ በስራ ላይ

‘ሌዝቢያን’ መሆኔን የተረዳሁት በአንድ አጋጣሚ ሣይሆን በሂደት ነው። የ13 ዓመት ልጅ እያለሁ ለአንዲት ሴት ጓደኛዩ ፍላጎት እያደረብኝ መጣ። መጀመሪያ ላይ እንደዚህ ዓይነት ስሜት (የፍቅር) ለተመሳሳይ ፆታ ጓደኛ ሲኖር የተለመደ መሆኑን ተጠራጥሬ ነበር። እንደመታደል ሆኖ ከኔ ክፍል ትይዩ አንዲት ላወራት የምችል በግልጽ “ባዮሴክሹዋል” እንደሆነች የሚታወቅ ልጅ ነበረች። የተለያየ ክፍል ስለሆንንና የተለያየ የጓደኛ ግሩፕ ስላለን ትምህርት ቤት ውስጥ ጓደኛ አልነበርንም፤ ፌስቡክ ሜሴንጀር ላይ ግን በደንብ እናወራለን።

ለጓደኛዩ ስለነበረኝ ስሜት ነገርኳት፤ ይህ ነገር ከተለምዷዊ ጓደኝነት የተለየ ነገር ይሆን እንደሆን ጠየኳት። ወሬያችን ያለኝ የፍቅር ስሜት እንደሆነ አረጋገጠልኝ። እንደዚህ ዓይነት ነገር ልክ እንዳልሆነ እየተማርኩ ስላደኩ፤ ለሴት ልጅ ፍላጎት እንዳለኝ ማወቄ ለኔ ከባድ ነበር።

> **“**
>
> **ቅርቤ ለሆኑ ሰዎች ስለፍቅር ግንኙነቴ ማጋራት አለመቻል በጣም ህመም ነበረው፤ ያም ሆኖ ግን ግንኙነቱ በራሱ “ሌዝቢያን” መሆኔን በደንብ አረጋገጠልኝ።**

በወግ አጥባቂ ሃይማኖተኛ ቤተሰብ ውስጥ ነው ያደኩት እናም እናቴና ሌሎች ዘመዶቼ “ሆሞፎቢክ” ነበሩ። ስለዚህ እንደሚጠበቀው ለቤተሰቦቼ ስለዚህ ጉዳይ ማውራቱ ለኔ አስፈሪ ነበር። ይህ ላሳልፈው የሚገባ ጊዜ እንደሆነ ተስፋ አድርጌ ወሲባዊነቴን ለመደበቅ ሞከረኩ።

16 ዓመት እስኪሞላኝ ‘ኦንላየን’ ላይ ካለችው ጓደኛዩ በስተቀር ስለጉዳዩ ከማንም ጋር አውርቼ አላውቅም። ያም ብቻ አይደለም ለወደድኳት ልጅም ለሷ ስሜት እንዳለኝ ለመንገር በጣም ፍርኃት ነበረብኝ፤ ምክንያቱም ብትስቅብኝስ ወይም ደ’ሞ ትምህርት ቤት ላሉት ሁሉ ስለጉዳዩ ብትነግርብኝስ ብዬ አሰብኩ።

16 ዓመት ሲሞላኝ በጣም ጓደኛዩ የምላት ልጅ “ሌዝቢያን” እንደሆነች ግልጽ አደረገችልኝ እናም በጣም የመገላገል ስሜት ተሰማኝ። እኔም ሴቶችን እንደምወድ ነገርኳት፤ የቅርብ ጓደኞቻችን ተቀበሉን። አጋጣሚው እንደኔ ዓይነት ሌሎች ሰዎች እንዳሉ እና ጓደኞቼም እንደማይተውኝ እንድረዳ አገዘኝ። ያም ብቻ አይደለም ስሜቱ ከዓመታት በኋላም ቢሆን አብሮኝ ስለቀጠለ ወሲባዊነቴ የአንድ አጋጣሚ ዐላፊ ስሜት ብቻ እንዳልሆነ ተረዳሁ። ስሜቴን እንድቀበል የረዳኝ ነገር ቢኖር የ“ሌዚቢያን” ግንኙነት ያላቸው ባህሪያት የሚታይበት የቴሌቭዥ ሾዎች ማየቴ ነው።

አሁን ኻያዎች ውስጥ እንዳለች አንዲት ወጣት፤ ስለወሲባዊነቴ በጣም ልበ-ሙሉነት ይሰማኛል። ከቤተሰቤ የደበኩትን የመጀመሪያዬ የሆነውን የፍቅር ግንኙነት የኖረኝ ከአንዲት ሴት ጋር በ19 ዓመቴ ነበር። ቅርቤ ለሆኑ ሰዎች ስለፍቅር ግንኙነቴ ማጋራት አለመቻል በጣም ህመም ነበረው፤ ያም ሆኖ ግን ግንኙነቱ በራሱ “ሌዝቢያን” መሆኔን በደንብ አረጋገጠልኝ። ከዛ በኋላ ለቤተሰቦቼ ግልጽ አደረኩላቸው፤ ምንም እንኳን ለነሱ ከባድና ያልተጠበቀ ቢሆንም ድጋፋቸውና ተቀባይነታቸው አልተለየኝም። ስለመጀመሪያዋ ፍቅረኛዬ ለታናናሾቼ ነገርኳቸው፤ ለቤተሰቦቼም ስነግራቸው በጣም ደጋፊዎቼ ነበሩ። በጊዜው የነበረችውን ፍቅረኛዬም ቤተሰቦቼ ተዋወቋት፤ ይህ ለኔ እንደ አንድ ታዳጊ በጭራሽ የማልጠብቀው ነገር ነበር። አሁን አንድ ወጣቶችን ስለ“LGBTQ+” ማኅበረሰብ የሚያስተምር ፕሮጀክት ላይ የራሴንም ልምድ በማካፈል እየሠራሁ እገኛለሁ።

# የፍርድ ቀን





አዲስ አበባ ላይ ጠዋት ማለዳ ነበር። በጊዜው ፍቅረኛዬ ከነበረችና ምሽቱን ከኔ ጋር ካሳለፈች ልጅ ጋር አልጋ ውስጥ ተቃቅፈን ነበር ወንድሜ የመኝታ ቤቱ በር ጋር ደርሶ የሆነ "ደህና አደራችሁ" ዓይነት ነገር ሲያሰማ፤ ከዛ የበሩን ሁለት ጊዜ መንኳኳት ተከትሎ የበሩ ዘንግ ሲዞር ሰማሁ። በሩን መዝጋት ረስቼው ነበር። ወንድሜን የምታውቀው ፍቅረኛዬ የበሩን መከፈት ስትሰማ ተደናግጣ ብርድ ልብስ ውስጥ ራሷን ደበቀች፤ እኔንም ጎትታ አስገባችኝ። ከብርድ ልብስ ውስጥ እንዳልወጣ አጥብቃ ለመነችኝ፤ እንደጠየቀችኝ አደረኩ።

ጫማዋ፣ የእጅ ቦርሳዋና ልብሶቿ ሶፋ ላይ ነበሩ። ወንዳወንዳዊ ነገር ስላለኝ በስህተት እንኳን አንዳቸውም የሷ ይሆናሉ ብሎ ወንድሜ እንደማያስብ ገብቶኛል። ወደ ክፍሉ ውስጥ ሲገባ ስላልሰማሁት ወይም ሌላ ጊዜ እንደሚያደርገው የመጣለትን ነገር ስላልተናገረ በር ላይ ቆሞ ሊሆን እንደሚችል አሰብኩ። ሰዓታት የሚመስለው (በርግጥ ቢበዛ አንድ ደቂቃ ቢሆን ነው) ጊዜ እንዳለፈ በሩ ሲዘጋ ሰማሁኝ። ከደቂቃዎች ዝምታ በኋላ ፍቅረኛዬ በሩን እንድዘጋው ጠየቀችኝና ክፍል ውስጥ ለሁለት ሰዓት ያህል ቆየን፤ ምክንያቱም ወንድሜ በርግጥም ከቤት ወጥቶ መሄዱን ማረጋገጥ ፈልጋ።

በተደጋጋሚ ላረጋግጥላት ብሞክርም፤ አልጋ ውስጥ ካገኘን ከቀናት በኋላ በጉልበት ቤተ-ክርስቲያን ወስዶን ኃይማኖታዊ መፍትሔ ሊፈልግልን ወይም ለቤተሰቧ ሊናገር ካልሆነም እኔን እዚህ ነገር ወስጥ በመክተቷ እሷን ሊወቅስ ባስ ሲልም ለፖሊስ ሊጠቁምብን እንደሚችል በማሰብ... እና ሌሎችም ቢሆኖችን እያሰበች ተጨነቀች።

ምንም ነገር አለማድረጉ ደሞ ወደሌላ ጥያቄና ጭንቀት አመራት። የሆነ ነገር ከሷ እየደበኩ እንደሆነ አሰበች። የሆነ ነገር በርግጠኝነት እንዳለኝና ያንን ለሷ ባለመንገር ከህመም ልጠብቃት እየሞከርኩ እንዳለሁ አሰበች። ምንም ነገር እንዳላለኝ ለሷ ለማሳመን ረጅም ጊዜ ወሰደብኝ።

ከዛ ደ'ሞ ወደሌሎች ጥያቄዎች ተሸጋገረች። ከዚህ በፊት ለወንድሜ ግልጽ ሆኜለት ዐውቅ እንደሆን ጠየቀችኝ። ምንም እንኳን ሊያውቅ ወይም ቢያንስ ሊጠረጥር ቢችልም በግልጽ ከሱ ጋር አውርቼ እንደማላውቅ ነገርኳት።

ለቀናት የሆነ ነገር ይፈጠራል ብላ ስትጠብቅ ቆየች። ምንም አልተፈጠረም። ወንድሜ እኔንም ሆነ እሷን የሚያናግርበት መንገድ ምንም አልተቀየረም።

በመጨረሻም እንዴት አንድ ኢትዮጵያዊ ወንድም እኅቱን ከሌላ ሴት ጋር አልጋ ውስጥ አግኝቶ የሆነ ጉልበተኛነት ነገር እንዳላሳየ ጠየቀች።

"
በመጨረሻም አንዴት አንድ ኢትዮጵያዊ ወንድም እኅቱን ከሌላ ሴት ጋር አልጋ ውስጥ አግኝቶ የሆነ ጉልበተኛነት ነገር እንዳላሳየ ጠየቀች።

ስለሌሎቹ ወንድም ዐላውቅም የኔ ወንድም ግን በጭረሽ እኔም ላይ ሆነ ኩዊርነቴ ላይ ከባድ ቃላትም ሆነ ጉልበት እንደማያሳይ ነገርኳት።

ለወንድሜ በግልጽ ነግሬው ባላውቅም፤ ስለራሴም ከሱ ለመደበቅ ብዬም ምንም ጥረት አድርጌ አላውቅም። በርግጥ አንድ ነገር ርግጠኛ ነኝ፤ ሁሌም ቢሆን እንደሚደግፈኝ። ቤተሰብ ማለት ለኔ ይሄ ነው፤ እርስ በራስ መደጋገፍ፣ መዋደድና መከባበር። እነዚህ ናቸው እኔና ወንድሜ ዋጋ የምንሰጣቸው ነገሮች።

ለወንድሜ ስለኩዊርነቴ ማብራራት አልፈልግም፤ ስለነገሩ መሟገትም እንደዛው። ማብራራት የሚፈልግ ጉዳይ አይደለም። በቃ ራሴን ነበርኩ፤ ሕይወቴን ያለምንም ማቅማማት የምኖር።

በጊዜው ወንድሜ "ሄትሮሴክሹዋል" ስላለመሆኔ ምንም ዓይነት ማብራሪያ ወይም ማረጋገጫ ቢፈልግ፤ ከሌላ ሴት ጋር አንድ አልጋ ላይ ማግኘቱ በቂ ማብራሪያ ይሰጠዋል። ከፍቅረኛዬ ጋር ባስተዋውቀው እፈልግ

ነበር፤ ግን የሷን ፍላጎት ማክበር ነበረብኝ።

ወንድሜ ሊለው ወይም ምናልባትም ሊያደርገው የሚችለው ነገር ከወራት በኋላም እንኳን ግንባር ቀደም ጭንቀቷ ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የ"ሆሞሴክሹዋል" ጥላቻ የሚፈጥረው ሥጋት፣ ፍርሃትና አሳሳቢነቱን ብጠብቀውም፤ የወንድሜ ድርጊትና ዝምታ ብዙ ሊነግራት ሲችል በዛ መጠን ርግጠኛ ለመሆን ያላት ማመንታትና ሁኔታዋ ጨርሶ ሊገባኝ አልቻለም።

ቤተሰቦቿ "ሆሞፎቢክ" ነበሩ፤ ስለዚህ የኔና የሷ ግንኙነት በሚስጥራዊነት የተደበቀ ነበር። የኔና የሷ ግንኙነት ላይ ቤተሰቧ ጥርጣሬ አሳድረዋል እናም አብረን ጊዜ እንዳናሳልፍ መረጡ። ከቤተሰቧ ፍላጎት በተቃራኒ መገናኘታችንን ቀጠልን እናም ቤተሰቧ ይህን እንዳያውቅ ጠንቃቃ ነበርን፤ ማለትም ዐልፎ ዐልፎ ብቻ እንደምንገናኝ ማስመሰል ነበረባት።

አንድ ምሽት ላይ ከሥራ ቦታዋ ለዕራት ይዣት ወጣሁና ዝም ብለን ከተማው ውስጥ አምስት ሰዓት ሊሞላ ጥቂት እስኪቀረው ተሽከረከርን። ምሽታችን ወደማለቁ ሲቃረብ አንድ ወንድ ጓደኛዋ ጋር ደውላ ቤቷ እሱ እንዲጥላት ሃሳብ አመጣች። ቤተሰቦቿ ከኔ እንድትርቅ ስለሚሞኙ የኔን ቤቷ ድረስ የመሸኘት ድግግሞሹ ላይ ሁሌም ቢሆን ጠንቃቃ ነበርን። ቤተሰቦቿ የዚህን ያህል መሽቶ ከቤት ውጪ እንደማይሆኑ አስባለሁ፤ ስለዚህ ጥንቃቄዋ ቅጥ ያጣ ይመስላል፤ ነገር ግን ከጥንቃቄዋ በተቃራኒ መቆም አልፈለኩም።

በነጋታው ፍርሃት በተሞላ ድምፅ ደወለችልኝና የኔ ቤቷ ድረስ ያለመሸኘት ሕይወት አድን ርምጃ ያህል እንደነበር ነገረችኝ። ልክ ከመኪና ስትወርድ ወንድሞቿ በእኅቶቿና በቤተሰቧ አነሳሽነት እየጠበቋት ነበር፤ እኔ ከመኪና ሳወርዳት እጅ ከፍንፍ ለመያዝ አስበው እንደነበር ነገሯት።

እናም በመጨረሻም አጋጣሚው ስለወንድሜ ያላትን ፍርሃት ስሜት የሚሰጥ አደረገው። ምንም እንኳን ለኔ በሌላ መልኩ ለሳም ጭምር ወንድሜ በዝምታውም ቢሆን የፈለግነውን ዓይነት ሕይወት እንድንኖር እኛን መቀበሉን ቢያሳይም፤ እሷ ግን የሱን ነፃ ሰውና ተቀባይ መሆን ቦታ ልትሰጠው አልቻለችም ነበር።

ወንድሞቿን በወንድሜ ውስጥ ነበር ያየቻቸው። አሰብኩት እነሱ ቤት እንዴት አድርገው በድንጋይ ሊቀበሉኝ እንደሚችሉ እና በመጨረሻም እኛ ቤት እጃቸውን ዘርግተው መቀበላቸው ግራ አጋቢ እምደሆነ አረጋገጠልኝ።

ወንድሜ ወደ መኝታ ቤቴ የመጣበት አጋጣሚ ለመጨረሻ ጊዜ እኛ ቤት ያደረችበት ነው። ምናልባትም የግንኙነታችን የመጨረሻው መጀመሪያ ሊባል ይችላል። ከዛ በኋላ ጥቂት ዓመታት ብቻ ነው አብረን የቆየነው። ጨርሶ አምርራ ራሷን ደበቀች እናም ውስጧን ዘልቆ የተዋሃደው "ሆሞፎቢያ" እሷ ላይና ግንኙነታችን ላይ የተጫወተው ሚና ይታየኛል።


በሌላ በኩል እኔ ወንድሜንም ሆነ ቀሪ ቤተሰቡን ማመስገን ወይም ከዛም በላይ እንዳለብኝ ተማርኩ። ያም ብቻ አይደለም ምንም እንኳን ጊዜ ቢወስድም አጋጣሚው ከእኅትና ወንድሞቼ እንዲሁም ከልጆቻቸው ጋር ስለወሲባዊነቴ ረጅምና ግልጽ ውይይት ማድረግ እንዳለብኝ አስወሠነኝ። ዝም ብዬና ምንም መናገር ሳይጠበቅብኝ የወንድሜን ተቀባይነት ማግኘቴ በጣም ምቾት የሚሰጥ ነገር ነበረው፤ ነገር ግን የታይታው ነገር አስፈላጊነት በዛ ቀን ወንድሞቿና ቤተሰባ ባሳዩት የኃይል ድርጊት ግልጽ ሆኗል።

ወንድሜ ከሌላ ሴት ጋር አልጋ ውስጥ ያገኘኝ ቀን መልካም ራስን የመግለጥ ተሞክሮ ነበር፤ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ላለው ጥላቻ ያለው እንቢተኛነት ለፍርድ የሚቀርብበትና በሰብዓዊነቱ የሚመሰገንበት ቀን ነበር።

> **"**
>
> **ወንድሜ ከሌላ ሴት ጋር አልጋ ውስጥ ያገኘኝ ቀን መልካም ራስን የመግለጥ ተሞክሮ ነበር፤ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ላለው ጥላቻ ያለው እንቢተኛነት ለፍርድ የሚቀርብበትና በሰብዓዊነቱ የሚመሰገንበት ቀን ነበር።**

# ራስ መቀበልን
## ማሳደግ





ተወልጄ ያደኩት አንድ የክልል ከተማ ውስጥ ነው። አባቴ የሁለት ዓመት ልጅ እያለሁ ነው የሞተው፤ እናቴ ድጋሚ ስላላገባች እኅትም ሆነ ወንድም የለኝም፤ ቤት ውስጥ ያለነው እኔና እናቴ ብቻ ነን።

እኔ ከጓደኞቼ ለየት እንደምል ማወቅ የጀመርኩት ገና 16 ዓመቴ አካባቢ ነበር። በሰዓቱ ስለ“ሆሞ ሴክሽዋልነት” ምንም የማውቀው ነገር ስላልነበር ብዙም አላሳሰበኝም። በጣም የቅርቤ የሆነች አንድ ጓደኛ ነበረችኝ፤ ለሱዋ ያለኝ ስሜት ከጓደኝነት በላይ መሆኑን ሳስተውል በጣም እየጨነቀኝ መጣ። ከሷም ለመራቅ ሞከርኩኝ፤ ግን ምንም የተቀየረ ነገር አልነበረም። ከዚህ ሁሉ በላይ ያስጨነቀኝ ነገር በሁኔታው በትክክል መማር ራሱ አለመቻሌ ነው።

“ምናልባት የወንድ ጓደኛ ቢኖረኝ ይሄ ሁሉ ነገር ይጠፋ ይሆናል” ብዬ ስላሰብኩ በሰዓቱ አብሬው እንድሆን ይጠይቀኝ ከነበረ ልጅ ጋር ሆንኩኝ። በጣም በጥሩ ሁኔታ ይንከባከበኝና ያከብረኝ ነበር። ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ምን ያክል እንደሚወደኝም ያሳየኝ ነበር። እኔም ላፈቅረው በጣም ሞክሬያለሁ፤ ግን ከማክበርና ከእኅታዊ መውደድ ውጪ ምንም ዓይነት የፍቅር ስሜት ሊሰማኝ አልቻለም። ጭራሽ ሊስመኝ ወይም ደ’ሞ የሆነ ነገር ለማድረግ ሲሞክር በጣም ምቾት አጣለሁ።  የሚሰማኝ ስሜት ከእናቴ ልጅ ጋር ግንኙት እያደረኩ ያለሁ

“

**ከዛ በኋላ ሕይወቴ ሁሉ ዝብርቅርቅ አለ። ጓደኛዬ ጠላችኝ ብቻ ሳይሆን ተጠየፈችኝ፤ ድጋሚ አጠገቧ እንዳልደርስ ይህ ካልሆነ ግን ለሁሉም የክፍል ልጆች እንደምትነግርና ከትምርት ቤትም እንደምታስባርረኝ ነገረችኝ።**

ያህል ይቀፈኛል። ሁኔታዎች ለትንሽ ጊዜ እንደዛ ቀጠሉ። እሱም ለሱ የፍቅር ስሜት እንደሌለኝ እየገባው መጣ፤ እኔም ማስመሰሉ ሰለቸኝ፤ ጨርሶ ደስተኛ አልነበርኩም። እሱንም እየዋሸሁት ያለሁት ነገር ሰላም ነሳኝ፤ በመጨረሻም ከሱ ጋር ያለኝን ነገር አቆምኩት።

አሁንም ምንም አልተቀየረም። ሴቷ ጓደኛዬ ለምን ከሷ ጋር ጓደኝነት እንዳቆምኩ "ምን በድዬሽ ነው" የሚል ጥያቄዋም ስላስጨነቀኝና በጣም የምቀርባት ጓደኛዬም ስለሆነች ጭምር ለሷ ያለኝን ትክክለኛ ስሜት ከዚህ በላይ መደበቅ እንደሌለብኝ ወሥኜ ነገርኳት። ከዛ በኋላ ሕይወቴ ሁሉ ዝብርቅርቅ አለ። ጓደኛዬ ጠላችኝ ብቻ ሣይሆን ተጠየፈችኝ፤ ድጋሚ አጠገቧ እንዳልደርስ ይህ ካልሆነ ግን ለሁሉም የክፍል ልጆች እንደምትነግርና ከትምርት ቤትም እንደምታስባርረኝ ነገረችኝ። በቃ መማር አልቻልኩም፤ ያኔ 10ኛ ክፍል ከጀመርኩ ገና ሦስት ወር አካባቢ ቢሆነኝ ነበር። ትምህርቴም ላይ ሆነ ባጠቃላይ ምንም ነገር ላይ ማተኮር አልቻልኩም። ትምህርት ቤት መሄድም ፈራሁ፤ ለእናቴ ከእንግዲህ መማር እንደማልችል እና እሷን ሠርቼ መርዳት ስለምፈልግ ዐረብ ሀገር እንድትልከኝ አልቅሼ ለመንኳት፤ እሺ አለችኝና ገንዘብ ከአጎቷ ተበድራ ላከችልኝ። እዛ ሄጄ እንደምንም ዓመት አካባቢ ብሠራም አዕምሮዬ ጥሩ ስላልነበረ ተመለስኩ።

ለእናቴ ሌላውን ነገር ሳልናገር ጭንቀት እንዳለብኝ ብቻ ነግሬያት አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ቦታ ቁርዐን እንዲቀራልኝ አደረኩ። ለሁለት ወር በተከታታይ ቢቀራልኝም ግን የነበሩኝ ስሜቶች (ለሴቶች ያለኝ ስሜት) አለመቀየሩን ሳውቅ በጣም መጥፎ ስሜት ውስጥ ገባሁ። እራሴን ምን ያህል እጠላው እንደነበር መግለፅ አልችልም። እስከመቼ የቆሻሻነት ስሜት እየተሰማኝ መኖር እንዳለብኝ ሳስብ ይበልጥ ሁሉም ነገር ይከብድብኛል። እራሴን ማጥፋትም ብዙ ጊዜ አስቤዋለሁ፤ የእናቴን ሁኔታ ሳይና ያለእኔ ማንም እንደሌላት ሳስብ ግን ለማድርግ ዐቅም አጣለሁ።

> **"**
>
> **እራሴን የመቀበሉ ጉዞ የእውነት የጀመረው እዚያ ከሄድኩኝ (ዐረብ ሀገር) በኃላ ነው። ኢንተርኔት እንደ ልቤ አገኝ ስለነበር ለሴት ልጅ ስላለኝ ስሜት ማንበብ ጀመርኩ። አለም ላይ እንደኔ አይነት መአት ሰዎች እንዳሉ ሳውቅ ምን ያክል ውስጤ እንደተደሰተ . . .**

ከሦስት ወር በኋላ በድጋሚ መሞከር ፈልጌ ጓደኛ ያዝኩኝ፤ ምንም ዓይነት የፍቅር ስሜት ግን አልነበረኝም። ከጊዜ በኃላ ሽማግሌ ተልኮ ቀለበት አሠርኩ። አሁንም ቢሆን ውስጤ ምንም ደስተኛ አልነበረም። ማታ ማታ ብቻዬን አለቅስ ነበር። ለማንም መንገር እንኳን አልቻልኩም ነበር። ጭንቀቱ እየባሰብኝ ሲመጣ የሱንም ሕይወት ከማበላሽ ብዬ ከመጋባታችን በፊት ተለየሁት።

ከሱ ጋር ካቆምኩ በኋላ "በዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ የኔ ጥፋት ምንድነው? ለምንድ ነው እንደዚህ ሆኜ የተፈጠርኩት?" ስለሚለው ማሰብ ጀመርኩ። በጣም በብዙ መንገድ ሳስበው የኔ ጥፋት እንዳልሆነ፤ ፈጣሪ ከሆነም የፈጠረኝ እንዲህ ሆኜ ለመፈጠሬ ተጠያቂውም ፈጣሪ ነው። ግን ደሞ ሳስበው ፈጣሪ አይሳሳት አይደል? "ምናአልባት እንዲህ ሆኜ መፈጠሬ ስህተት አይደለም ይሆን? ሌላስ እንደኔ ዓይነት ሰዎች አሉ ይሆን" የሚሉ ጥያቄዎች ይፈጠሩብኝ ጀመር። ለሴቶች ስላለኝ ስሜት ብዙ ማወቅ ፈለኩ "ግን ከማን ጋር ልወያይበት? ያሉኝን ጥያቄዎችስ ማንን ልጠይቅ? ምንስ ብዬ ነው የምጠይቀው?" ሳስበው ለራሴ የሚቀፈኝን ነገር እንዴት ለሰው አወራዋለሁ? በዚህ መኻል እርጉዝ መሆኔን ዐወኩ እናም ሀሳቤ ወደ እርግዝናዬ ዞረ። እናቴ እርጉዝ መሆኔን ስታውቅ በጣም ደስተኛ ስለነበረች ወሬያችንም ሀሳባችንም ሁሉ ስለልጅ ሆነ፤ በመጨረሻም መንታ ልጆች ወለድኩ። የልጆቹ አባት ከሱ ጋር የነበረንን ነገር በማቆሜ ምክንያት ሊያናግረኝም ሆነ ሊያገኘኝ ስላልፈለገ ልጆቼን ብቻዬን ማሳደግ ነበረብኝ፤ ለዛ ደሞ የግድ መሥራት ነበረብኝ፤ ስለዚህ ልጆቹ ሦስት ወር ሲሞላቸው ለእናቴ ሰጥቻቸው ወደ ዐረብ ሀገር ሄድኩ።

እራሴን የመቀበሉ ጉዞ የእውነት የጀመረው እዚያ ከሄድኩኝ በኃላ ነው። ኢንተርኔት እንደ ልቤ አገኝ ስለነበር ለሴት

ልጅ ስላለኝ ስሜት ማንበብ ጀመርኩ። ዓለም ላይ እንደኔ ዓይነት መዓት ሰዎች እንዳሉ ሳውቅ ውስጤ ተደሰተ፤ ያ ማለት ግን አሁንም ቢሆን “ሌዝቢያን” መሆኔ ልክ ነው ብዬ ተቀብዬ አይደለም። “ይህ ችግር እኔ ብቻ አይደለሁም ያለብኝ ማለት ነው ?!” የሚል ስሜት ነው የተሰማኝ። በተወሠነ መልኩ አጽናኝ ነበር። ከዛም “youtube” ላይ ስለተመሳሳይ ፆታ ፍቅረኞሞች ማየት ጀመርኩ። ምን ያህል ነፃነት የሚሰማቸው እንደሆኑ ሳይ እገረም ነበር። “እንዴት እንደ ጥሩ ነገር እንዲ ገሀድ ያወጡታል?!” ብዬም ይደንቀኝ ነበር።

የሆነ ቀን አንድ ቪዲዮ ዐየሁ። አንድ ሰውዬ “ሰዎች ፈልገውና መርጠው ነው ‘ጌይ’ የሚሆኑት እና የምርጫ ጉዳይ ነው” ነበር የቪዲዮው ይዘት። ዓይኔን ያበራልኝ ያ ቪዲዮ ይመስለኛል፤ ምክንያቱም ያ ሰውዬ ምን ያክል እንደተሳሳተ ጠንቅቄ ዐውቃለኍ። “ሌዝቢያን” ለመሆን መርጬም ፈልጌም በፍፁም ዐላውቅም። ይሄን ውስጤም በደንብ ያውቀዋል። ስለዚህ “መርጬ እና ፈልጌ ላልሆንኩት ነገር ለምን ራሴን ጠላዋለሁ?” የሚል ጥያቄ ውስጤ ተፈጠረ። በዛ በላይ ደሞ እራሴን እንድጠላው ከሚያደርጉኝ ሀሳቦች አንዱ “ፈጣሪ ይጸየፈኛል” የሚለው ሀሳብ ነበር። ግን “እራሱ እንዲህ አድርጎ ፈጥሮኝ እራሱ ለምን ይጠላኛል? እሺ እንዲህ እንዳልሆን ከፈለገ ለመቀየር በጣም የለመንኩት ጊዜ ለምን አልቀየረኝም?” ብዬም አሰብኩ። “እንድቀየር ባይፈልግ ይሆናል ፈጣሪ አይሳሳትም” በሚለውም አምናለሁ። ስለዚህ “እኔንም እንዲህ አድርጎ ሲፈጥረኝ ወዶ እና ፈቅዶ እንጂ ተሳስቶ አይደም” ብዬም አሰብኩ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ “እራሴን እንዴት ልለውጠው” ሣይሆን “ከራሴ ጋር እንዴት ሰላም ልፍጠር” ስለሚለው ማሰብ ጀመርኩ። ብዙ ሀሳቦችን በተመሳሳይ ፆታ ዙሪያ የተጻፉ ጽሑፎችን ማንበብና ቪዲዮዎችን ማየት ጀመርኩ። ቀስ በቀስም ምንም ችግር እንደሌለብኝ እና ለሴቶች ያለኝም ስሜት አንድ ሴት ለአንድ ወንድ እንደሚኖራት ዓይነት ፍቅር የኔም ለሴት ያለኝ ስሜት የዛኑ ያህል ጤነኛና ንጹሕ እንደሆነ እያመንኩ መጣሁ። ግን አሁንም አንድ ጥያቄ ውስጤ ነበር “ለምንድን ነው ዓለም ላይ ያሉ አብዛኞቹ ሰዎች ‘ጌይ’ መሆን ኃጢያት ነው የሚሉት? እኛ ‘ጌይ’ የሆንነውስ ለምንድን ነው ራሳችንን የዚን ያክል የጠላነውስ?” የሚለው ነው። ከብዙ ማንበብ እና ብዙ ቪዲዮዎችኝ ከማየት በኋላ የተረዳሁ ነገር ቢኖር የሰው ልጅ ምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ባህሎች፣ዕምነቶችንና ሀሳቦችን አስተናግዷል፤ እየቆየ ሲመጣም ብዙዎቹን ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ስለሚበልጥ ትቷቸዋል። ለብዙዎች የሚጠቅሙት ደ’ሞ ይበልጥ ጎላ ብለው ወጥተው ታይተዋል። አንድ ጊዜ ምድር ክብ መሆኗ እስከተረጋገጠበት ጊዜ ድርስ ጠፍጣፋ ናት ተብሎ ይታመን ነበር አሉ “ጌይ መሆን ኃጢያት ወይም በሽታ ነው” የሚለው ዕምነትም እንደዛው ነው።

አሁን ላይ በአንጻራዊነት ብዙ ሰው “ጌይ” መሆን ኃጢያትም ሆነ በሽታ አለመሆኑ እየገባው ስለመጣ፤ ብዙ ቦታዎች ላይ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ከድሮው በተሻለ በነፃነት ሕይወታቸውን እየኖሩ ነው። እኛም እራሳችንን የመጥላት ስሜት የሚፈጠርብን፤ ስንሰማው የኖርነው ኃጥያት መሆኑን ስለሆነና እኛም ኃጥያት ነው ብለን ስላመንን ነው። ተፈጥሮሽ የሆነን ነገር እራስሽ መጥላት በጣም ከባድ እና አስጨናቂ ነው። ከዛ ስሜት እንደመገላገል ዕረፍት የለም።

አሁን እራሴን አልጠላም፤ እንደውም በራሴ በጣም እኮራለሁ። ያንን ሁሉ ከራስ ጋር ጥል ዐልፌ ዛሬ ላይ ከራሴ ጋር ተስማምቼ ሳይ በራሴ እኮራለሁ። ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ያልሆኑ ሰዎች የሆነውን ሰው መጥላት ለነሱ በጣም ቀላል ነው። ስለ ወደፊቱ በማንነቴ ዙሪያ ምንም ዕቅድ የለኝም። ከባዱን ነገር ዐልፌዋለሁ። ሀገራችን ላይ የሆነ ተዓምር ተፈጥሮ ራሳችንን ሆነን የምንኖርበት ዕድል ቢሰጠንና የኔ የምላት ሴት ኖራኝ በነፃነት አብሬያት መሆን ብችል ደስ ይለኛ

> “
>
> **ሀገራችን ላይ የሆነ ተዓምር ተፈጥሮ ራሳችንን ሆነን የምንኖርበት ዕድል ቢሰጠንና የኔ የምካት ሴት ኖራኝ በነፃነት አብሬያት መሆን ብችል ደስ ይለኝ ነበር።**

ነበር። እኔ በድብቅ ፍቅረኛ ይዤ የመኖር ችሎታው ያለኝ አይመስለኝም። ስለዚህ ለወደፊቱ ማድረግ የምፈልገው ነገር ልጆቼ እንደሌላው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዓይነት አስተሳሰብ እንዳይኖራቸው፤ በተቻለኝ መጠን እነሱ ስለዚህ ጉዳይ ሙሉ ዕውቀት እንዲኖራቸው ማስተማር ነው። “ሌዝቢያን” በመሆኔ ከምደሰትበት ምክንያቶች አንዱ ከልጆቼ አንዱ “ጌይ” ቢሆንና መጥቶ ቢነግረኝ በደስታ ተቀብዬው “ጌይ” ካልሆነው ልጄ ዕኩል እንደምወደው ሳስብ ነው።

እስካሁን ግን ለማንም ሳልናገር ማንም ሳያውቅ ለራሴ በውስጤ ይዤው እየኖርኩ ነው።





# ሀዘን
# እና
# በዐል

# ጓደኛን ማጣት፥ ራስን ማግኘት

“

**አንድ ነገር ልነግርሽው ነው. . ከአይኔ ሊያመልጡ ያሉ እንባዎቼን ከመደበቅ አየታገልኩ: : እንዴት የቅርብ ጓደኛ እንደዚህ ያስፈራል? የማላውቃት ልጅ እንዴት ትሆንብኛለች?**

ከስራ ስትወጣ ቡና ለመጠጣት አዘውትረን እንገናኛለን:: አንዳንዴም አምሽተን እራት በልተን እንለያያለን:: ፒያሳ እና አራት ኪሎን በእግር እየተጓዝን የባጥ የቆጡን እያወራን ስንስቅ እናመሻለን:: ፊልም የማየት ምሽት እየተቀጣጠርን ስናወራ ፊልም ስናይ እናድራለን:: ቤተሰቦቼ ያውቋታል የእሷም ቤተሰቦች ያውቁኛል:: ለሰርጌ ሚዜዬ ለሰርግሽ ሚዜ ነኝ የመባባል ያህል ቅርርብ ያለው ጓደኝነት ነው ያለን:: ምንም አይነት ዜና ሲኖረን ቀድመን እንደዋወላለን:: በሳቃችን ሁሉ ውስጥ ቁምነገሮችንም ስናወራ እንውላለን:: በሴቶች መብት ዙሪያ ያለን አመለካከት ተመሳሳይ ስለሆነ ብዙ ጊዜ ስለጭቆና እያነሳን እናወግዛለን:: ከከተማ ወጥተን በጣም ደስ የሚል ጊዜ አሳልፈን እንመለሳለን:: ብቻ በጣም የምንዋደድ ጓደኛማቾች ነን::

ብዙ አመት አብረን በጓደኝነት ብናሳልፍም ሌዝቢያን መሆኔን ግን አልነገርኳትም:: ፍርሃት እንዳለ ቢሆንም በነበረው የራስ ትግል እና ጫና የወንድ “የፍቅር ጓደኛ” ስለነበረኝ በጊዜው መናገሩ አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም:: እሱን ታውቀዋለች አብረንም ብዙ እናሳልፋለን:: ከወንድ “የፍቅር ጓደኛ” ጋር አመታት ከታገልኩ በኋላ በተለየ ምክንያት ተለያየን:: የመጨረሻዎቹ አመታት ላይ ከራስ ጋር የነበረኝ ትግል ከባድ ነበር... ከቤቴ ጋር ዘወትር እየተገናኙ የውስጥን ትልቅ ውጣውረድ አለማካፈል ቀላል አይደለም:: እሷ ስለምታገኛቸው ወንዶች ስታጫውተኝ እኔ ደግሞ የሌለ ያለውን እያተራመስኩ እዋሻታለሁ:: የጥፋተኝነቱ ስሜት ያስጨንቃል::

ከፍቅር ግንኙነቱ ከወጣሁ በኋላ ራሴን የመቀበሉን ጉዞ በደንብ ጀመርኩ:: ለብዙ አመት አልቀይረው ያልኩትን የሴት ልጅ ተማርኮ እጄን ዘርግቼ መቀበል ጀመርኩ:: ስሜቴን ከራሴ ጋር መወያየት እና ራሴን በሹክብሹክታ “ሌዝቢያን ነሽ ምንም ችግር የለም” አልኩኝ::

በዚህ ሁሉ ውስጥ ቤቲ ምንም የምታውቀው ነገር የለም:: ከወንድ ጋር ግንኙነት ሲኖረኝ ተፈጥሮዓዊ ስሜት እንደማይሰማኝ፣ እንደሚሰለቸኝ አልፎም ከማግኘት አለማግኘትን እንደምመርጥ አታውቅም:: በተለያዩ አጋጣሚዎች ሴት ልጅ አልፎ አልፎ ልቤን ስርቃው እንደምታውቅ አታውቅም:: ዘወትር ግን እንገኛለን ስለውሏችን እንጠያየቃለን...ህይወቴ ላይ ምንም አይነት ጥያቄ እንደሌለብኝ ስስቅ አመሻለሁ:: እንቅልፍ አልባ ምሽትን አሳልፌ ደግሞ ቀኑን እደግመዋለሁ::

ምን እንዳነሳሳኝ አላስታውሰውም ቤቷን ከስራ በኋላ እንገናኝ ብያት የምናዘወትርበት ካፌ ቁጭ ብዬ መጠበቅ ጀመርኩ። እጅም እግሬም ይንቀጠቀጣሉ እልፍ እያለ ልቤም ፍጥነት ይጨምራል።

"ከምንድን ነው የምጀምረው?" ከራሴ ጋር እመካከራለሁ..ለማረጋጋት ደግሞ "በቃ እንደመጣልኝ አወራለሁ ምን አገባኝ" አላለሁ። ሳምሪዬ እቅፍ አደረገችኝ። የልብ ምቴ ማራቶን ላይ ነው። ድንብርብ ማለቴን ስላየች "ምንድን ነው የምትደናበሪው?" አለችኝ...አልመለስኩላትም። የምንጠጣውን አዘን እየጠበቅን "አንድ ነገር ልነግርሽው ነው".. ከአይኔ ሊያመልጡ ያሉ እንባዎቹን ለመደበቅ እየታገልኩ። እንዴት የቅርብ ጓደኛ እንደዚህ ያስፈራል? የማላውቃት ልጅ እንዴት ትሆንብኛለች? ውስጤ ሲግል ይሰማኛል..."ሳምሪዬ ደህና ነሽ?" እውነትም ከየት ልጀምር... "አንቺ እያጨናነቅሽኝ ነው..ምን ሆነሽ ነው?"

እንደምንም ቃል ወጣ "ወንድ 'ዴት' ማድረግ የምችል አይመስለኝም"... አላስጨረሰችኝም "አሁን ገና አይደል እንዴ የተለያየሽው.. ጊዜ ስጪ እንጂ"... አይኗን ላለማየት አንዴ ፀጉሯን..አንዴ ሌላ ጠረጴዛ ላይ ያሉ ልጆችን አያለሁ። "ቤቲዬ ለሴት የተለየ ታማርኮ አለኝ. ይሄንን ደግሞ ገና ድሮ ነው የማውቀው..." የፊቷ በቅፅበት መቀያየር ቀጥዬ እንዳላወራ አሰጋኝ። ፊቷ ደም ለብሷል..ለደቂቃዎች ምንም አላወራችም። የእሷ ድንጋጤ እና የቁጣ ፊት እንደአዲስ አስደነገጠኝ፤ ልቤ ተሸበረ።

የመጣው ማኪያቶ ሳይነካ.. በመሃላችን ፀጥታ ሰፍኖ ከቆየ በኋላ "እንዴ ምን ማለትሽ ነው? ከቶማስ ጋር የነበረሽ ግንኙነት አልተሳካም ማለት ለሌላ ወንድ ስሜት የለሽም ማለት አይደለም"... "ቤቲዬ እንደሱ አይደለም..." አቋረጠችኝ "የተለያዩ ግንኙነቶች ስላልተሳኩ እዚህ መደምደሚያ ላይ መድረስ ምን ማለት ነው? ምን እንደምልሽ ራሱ አላውቅም".. ድምፄን ዝግ አድርጌ "ሌዝቢያን ነኝ" አልኳት። የሹፈት ሳቅ ሳቀች... "በፍፁም አልቀበልም" ብዙ ተመላለስን... ለማስረዳት ሞከርኩ፤ አልተሳካልኝም። እንዴት ቻው እንደተባባልን አላስታውስም። ቤቴ ገብቼ በጣም አለቀስኩ፣ ጓደኝነት ምንድን ነው? ብዙ አወጣሁ አወረድኩ።

በነገርኳት ነገር በጣም እንደተጎዳች ደጋግማ ፃፈችልኝ። ምንም ጥያቄ አልጠየቀችኝም፤ አላዳመጠችኝም። ደጋግማ ሐጢያተኛ እንደሆንኩ እና ወደራሴ እንድመለስ ፃፈችልኝ። መልዕክቶቹን አነብና ደግሜ እንዳላነባቸው አጠፋቸዋለሁ። የለመድኩት "ሳምሪዬ ዛሬ የት እንሁን?" አይደሉማ! በጣም ልብ የሚሰብሩ ነበሩ።

በጣም ስለምንዋደድ ብቻ ሳይሆን የሴቶች መብት ዙሪያ ያላት ጠንካራ አቋም፥ አትቀበለኝም ቀርቶ ለማዳመጥ ይከብዳት ይሆናል የሚል ምንም ጥርጣሬ አልነበረኝም።

ለመጨረሻ ጊዜ ስመልስላት የተሰማኝን ሁሉ ነው የፃፍኩላት፥ በይበልጥ ያተኮርኩት ደግሞ "ምን አይነት ጓደኝነት ነው ለማዳመጥ እንኳን ቦታ የማይሰጠው?" "እንዴት ይሄ ሁሉ አመት ስንዋደድ አንድ ማንነቴ እዚህ ላይ አደረሰሽ?" ላይ ነበር። ከሷ መልስ አልነበረም።

ከዛ መልዕክት በኋላ በተደጋጋሚ እንሄድባቸው ከነበሩ ቦታዎች ጠፋሁ። የጋራ ጓደኞች ከሆኑን ጋርም ቀስ በቀስ ራቅኩኝ። የምወዳትን ጓደኞዬን ማጣት ቀላል አልነበረም። ለሌላ ሰው ለማስረዳት የሚከብድ አይነት መጎዳት ነበረው። ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው እንኳንም ነገርኳት፤ እንኳንም ሆነ እላለሁ። የቀረው ሁሉ ቀርቶ ራስን መምረጥ መቻል ትልቅ ትርፍ ነው።

> "
>
> **የምወደትን ጓደኛዬን ማጣት ቀላል አልነበረም : : ለሌላ ሰው ለማስረደት የሚከብድ አይነት መጎደት ነበረው። ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው እንኳንም ነገርኳት፤ እንኳንም ሆነ እላለሁ : : የቀረው ሁሉ ቀርቶ ራስን መምረጥ መቻል ትልቅ ትርፍ ነው።**



# ምቹ
# ቁምሳጥን

## “ቁምሳጥኔ ከሳሎኔ የበለጠ ምቹ ነው”

“ወሲባዊ ማንነትሽን መቼም ቢሆን ግልጽ ታደርጊያለሽ?” ቀላል ጥያቄ ከተወሳሰበ መልስ ጋር። በአንድ ወዳጄ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ አቀራረብ የሚቀርብልኝ ጥያቄ ነበር። “ከአንዲት ሴት ጋር ፍቅር ቢይዝሽስ፤ ለቤተሰቦችሽ ትነግሪያቸዋለሽ?” ወይስ “ከሀገር ብትወጪስ፤ ወሲባዊ ማንነትሽን  ግልጽ አድርገሽ ትኖሪያለሽ?” ከልብ ግልጽ ለመሆን በጭራሽ መልስ አልነበረኝም።

ለጓደኛቼ “ስለወሲባዊ ማንነቴ ግልጽ ያደረኩላቸው” ከዓመት ከመንፈቅ በፊት ፒዛ እየበላን በመኻል ስለ“ዴቲንግ” በምናወራበት ወቅት ነበር። እንዲ አልኳቸው “በነገራችን ላይ ምናልባት “ባይ” ነኝ፣ አላውቅም ብቻ፤ የማውቅም ነገር ሴት ደስ እንደሚለኝ ነው። ይመስለኛል በነገሩ በጣም ግራ ተጋብቻለሁ” እስካሁን ድረስ ሁኔታቸውን አስታውሳለሁ፤ የተለየ ነገር አድርገው አልነበረም። እስካሁን ድረስ ምን ያህል እንደሚወዱኝና ነገሩ በመኻላችን ያለውን ነገር ምንም እንደማይቀይረው ወይም ደ’ሞ በተቃራኒው ተሰምቷቸው ልክ ያልሆነ ነገር እንደሆነ አልነገሩኝም። በቃ ነገሩን ተቀብለው ጫወታችን ቀጠለ። ይህ ስለወሲባዊ ማንነቴ ግልጽ ያደረኩበት አደጋ የሌለወና ብቸኛው አጋጣሚ ነው። ጓደኞቼን ለዓሥርት ዓመታት ይሆነናል ሳውቃቸው፤ ምላሻቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ዐውቀዋለሁ። ፖለቲካቸው ይገባኛል፤ የት ላይ እንደቆሙ አውቃለሁ። ይህም ነው ለግማሾቹ  ጓደኞቼ ብቻ ግልጽ የማድረጌ ምክንያት፤ ቀሪዎቹ ግን “ባዮሴክሹዋል” መሆኔን አያውቁም፤ በቅርቡም ያውቃሉ ብዬ አላስብም።

ሁኔታው ላይ መወሰን የምችል ከሆነ፤ አባቴም ቢሆን ስለወሲባዊ ማንነቴ ሊያውቅ አይችልም። ይህን ውሣኔ የወሠንኩት ከረጅም ጊዜ በፊት ነው። አንድ ጊዜ በወሬ መኻል አባቴን ስለ“LGBTQ+” ምን እንደሚያስብ ጠየኩት፤ አብረን ዕናየው በነበረው ፊልም ውስጥ “ጌይ” ጥንዶች ካየን በኋላ እናም “ምንም አይደል፤ አልወቅሳቸውም፤ የነሱ ጥፋት አይደለም ሴጣን ነው። ወደ ገዳም ቢሄዱና ለሦስት ወር እዛ ቆይተው ፀበል ቢጠመቁ ሊሻላቸው ይችላል።” ሲል መለሰልኝ። ይህ ብቸኛው ጊዜ ነው ጉዳዩን ለውይይት ሳቀርበው፤ ከዛም እዛው ነበር የወሠንኩት፤ ለሱ ስለወሲባዊ ማንነቴ ግልጽ ባደርግለት መጨረሻዬ እጄ በሠንሠለት ታሥሮ አንድ ምድረበዳ ላይ ያለ ገዳም እንደሚሆን እያወኩ እንደማልነግርው።

ስለወሲባዊ ማንነት ግልጽ ማድረግ የራስ መንገድ ነው። በጣም ህመም የተሞላበት ውሣኔ ነው፤ የቱም ቢሆን በቀላሉ የሚወሰድ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ከፍላጎት ውጪ መብታቸውን ተነጥቀው ማንነታቸው የሚጋለጥበት ሁኔታ ነው ። ኢትዮጵያ ውስጥ ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ስለማድረግ ሳስብ ትልቅ አደጋ ነገር ግን ትንሽ ሽልማት የሚያስገኝ ቁማር አድርጌ ነው የማስበው። ወግአጥባቂ በሆነው በኛ ሀገር ሁሉም “ኩዊር” ማህበረሰቡ ስለመኖራችን ያለው ምላሽ አይጠፋውም ። በ“LGBTQ+” ላይ ያለው ጥላቻ ብቻ አየደለም፤ ጥላቻው በባህል፣ በኃይማኖት እንዲሁም ከምንም በላይ በሕግ የተደገፈ ነው። ስለዚህ ማሰብ ያለብን እኛ ላይ ስለሚያሳድረው ሥነ-ልቦናዊ ጫናው ብቻ አይደለም፤ ከዛ በተጨማሪ በሕይወታችን ላይ ሊከተል ስለሚችለው መዘዝም ጭምር ነው። ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድረግ ነፃነታችንን በብዙ መልኩ ዋጋ ያስከፍለናል። ምክንያቱም እንደ“ኩዊር” ግልጽ መውጣት ብቻ አይደለም ጉዳዩ፤ በወደድሽው ሰው ወይም በማንነትሽ ምክንያት በሕግ ፊት ወጀለኛ ሆኖ የመታየት ጭምር ነው። የሕይወት ዋጋ ሊያስከፍለን ይችላል። በገቢ ምንጫችን ላይ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ በነበረን ቦታ እና በጤናችን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። ስለዚህ እኛ እንደ“ኩዊር” ይህን እውነተኛና ህምም ያለው ጥያቄ ራሳችንን መጠየቅ አለብን: ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ በማድርግ የሚመጡት አደጋዎች ምንድን ናቸው፤ ዋጋ ሊከፈልላቸውስ የሚገቡ ናቸው? እኔ አይደሉም ባይ ነኝ፤ አንቺ የተለየ መልስ ሊኖርሽ ይችላል እናም ከልቤ አንቺ ልክ ብትሆኚ እመኛለሁ። ግን አይመስልኝም።

> “
>
> **ያንቺ ደኅንነት፣ ከኩራትሽና ወሲባዊ ማንነትሽን ግልጽ ከማድረግ በላይ ዋጋ አለው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ዋጋ የሚኖራቸው አንቺ እዚህ እስካለሽ፣ ጤና እስከሆንሽና በሕይወት እስካለሽ ድረስ ነው።**

ወጣት ኢትዮጵያዊ “ኩዊር” ብትሆኚና እንዴትና መቼ ወሲባዊ እኔነቴን ግልጽ ማድረግ አለብኝ ብለሽ የምትጠይቂኝ ብትጠይቂኝ፤ ፈጣን መልሴ ሊሆን የሚችለው ተይ የሚል ነው። መልሴ ፍርኀት የወለደው እንደሆነ ዐውቃለሁ፤ ግን ደ`ሞ ከፍርኀቴ ጀርባ ያለው አደጋ እርግጥና ትኩረት የሚሻ ነው። ሆኖም ግን ወሲባዊ ማንነትን ግልጽ ማድረጉ ላይ ጽኑ አቋም ካለሽ የምመክርሽ ነገር ቢኖር አማራጭ ዕቅድ እንዲኖርሽ ነው፤ የራስሽ የሆነ የገቢ ምንጭን ጨምሮ ልክ የምትኖሪበት ቦታና በዚህ ሁኔታ ውስጥ ካለፉ ሰዎች የሚገኝ ድጋፍና ምክር ማግኘት ያስፈልግሻል።

ያንቺ ደኅንነት፣ ከኩራትሽና ወሲባዊ ማንነትሽን ግልጽ ከማድረግ በላይ ዋጋ አለው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ዋጋ የሚኖራቸው አንቺ እዚህ እስካለሽ፣ ጤና እስከሆንሽና በሕይወት እስካለሽ ድረስ ነው። ስለዚህ  የመጀመሪያ ምክሬ ሊሆን የሚችለው ሁልጊዜ ደኅና መሆንና በሕይወት መቆየት ነው፤ ሌላው ከዛ በኋላ የሚከተል ነገር ነው።

በግሌ ወሲባዊ ማንነቴን ግልጽ ላለመውጣትና እንደሚባለኤ “ቁም ሳጥን” ውስጥ ለመቆየት ወሥኛለሁ። ነገር ግን ያን የኔን ድብቅ ዓለም ምቹ ማድረግ እፈልጋለሁ፣ ደኅንነት እንዲሰማኝ የሚያደርገኝ ቦታ እንጂ መደበቂያ እንዲሆን አልፈልግም። ጓደኞቼ መጥተው ሊጎበኙኝ የሚችሉበት፣ ሕይወቴን እንደምመኘው ሆኜ መኖር የምችልበት፣ ቆንጆዬ ሴት የምስምበት የዳንስ ድግስ የማዘጋጅበት እናም የሁሉም ሰው ትኩረት የሚሆነው በከለር ያሸበረቀ ጭምብል መሆኑ ላይ ብቻ እስከሆነ ድረስ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ የ“bi pride” ጭምብል ማድረግ፤ በራሴ ዓለም ውስጥ በነፃነት መኖርና ራሴን ሆኜ መገኘት። ስለዚህም ወሲባዊ ማንነቴን ግልጽ ማድረጉን በጥንቃቄና ሊከተል ከሚችል ማንኛውም ጉዳት የምጠበቅበትና ደኅንነት የተሞላበት ሂደት ማድረግ ላይ ነው ጥረት እያደረኩ ያለሁት። ያው አንድ ቀን ያለምንም ሥጋት በነፃነት ወሲባዊ እኔነቴን ግልጽ እንደማደርግ ተስፋ እያደረኩ፤ ነገር ግን እስከዛ ቀን ድርስ የኔ ዓለም ውስጥ በልባቸው ፍቅር ይዘው መምጣት ለሚፈልጉ ሁሉ በሩ በትንሹ ገርበብ ይላል።

# የኲዊር አጋር ማስታወሻ

## ለመቀበል የሚደረግ ቀስ ያለ፣ ቋሚ ጉዞ



ሁልጊዜም በህይወታችን ላይ አቅጣጫ ጠቋሚ ሰዎች አሉን። በማህበረሰብ፣ በቤተሰብ እና በአቅራቢያችን ባሉት ሰዎች ሁሉ ከተሰራልን አጥር ዘለን እንዳናስብ እንዳናይ ከተከለልንበት ውጪ ሆነው በጥቅሻ የሚጣሩ፤ በዚህም መንገድ አለ ብለው እግር ባልረገጠው ቁጥቋጦ የሚመሩ፤ አእምሮአችንን ተፈጥሮ ለማያልቅባት ለአዲስ ነገር ሁሉ ዝግጁ የሚያደርጉ ሰዎች አሉን።

አስታውሳለሁ ሁለተኛ ልጄን እርጉዝ ነበርኩ። እርግዝናዬ ከሌላው ግዜ በተለየ ሰነፍ አድርጎኝ ነበር፤ እንቅስቃሴ

የምጠላበት  እና ተኝቼ ሶሻል ሚዲያ ላይ ብዙ ሰአት የማጠፋበት ግዜ ነበር። በዛም ምክንያት ብዙ አይነት ችሎታ ያላቸው ከተለያየ ቦታ የተውጣጡ ጓደኞች ነበሩኝ። ጥሩ ስብስብ እና የማልወደውን መርጬ የማስወጣበት ፕላትፎርም ነበር። አንድ ቀን people you may know ላይ አንድ የሀበሻ ሰልካካ አፍንጫ እና ጠይም ደም ያለው ፣ ስቶኪንክ በሂል ጫማ ያደረገ ወንድ ልጅ ሲመጣልኝ ደነገጥኩ። ሆሞ ሴክሹዋሊቲ ብዙ መስማት ከማልፈልገው ወይንም ብዙ ትኩረት ልሰጠው ከማልፈልጋቸው ርእሶች ውስጥ አንዱ ነበር።

አእምሮዬ ሊመራመርባቸው ወይንም የበለጠ ሊያውቃቸው ከማይፈልጋቸው ርእስ መሃል ከትቶ እያለ እንደሌለ የረሳው ርእስ ነበር። በጣም የምወደው የውጪ ቴሌቪዥን ሲትኮም ሞደርን ፋሚሊ ላይ እንኳን የምወዳቸው ጥንዶች Cameron እና Mitchell ሆነው እንደፊልም ለደቂቃው ስቄ ከማለፍ በቀር በእውነታው አለም ስላለው ጌይ ወይ ሌዝቢያንነት እንደ ጥያቄ የሚያነሳውን ጎኔን የሚቀብር ትክክለኛ ቃሉ ከሆነ <<የመቅፈፍ>> ስሜት ብቻ ነበር  የነበረኝ። በዛም ምክንያት ለho-mosexuality  አይን የሚያቀላ ጥላቻም መውደድም አልነበረኝም። ትክክለኛ ስሜቴን መርምሬ አላውቀውም ነበር።

በተለይ ለሀገራችን ኢትዮጲያ የሩቅ ህልም እንጀራ እንጂ ማንም ኢትዮጲያዊ ሌዝቢያን ወይንም ጌይ ደፍሮ ከኖርንበት ባህል ሀይማኖት ተታግሎ፤ ራሱን አምኖ ተቀብሎ ፤ያውም ሶሻል ሚዲያ ላይ ራሱን ይፋ ያደርጋል ብዬ አላስብም ነበር። የልጁን ፕሮፋይል እንዳየሁት እንደታመመ ሰው አዘንኩለት። <<ምፅፅ ምን ሆኖ ነው?>> አይነት ስሜት ተሰማኝ። ቀጣይ ፕሮፋይሉ ውስጥ ገብቼ መበርበር ጀመርኩ ብዙ ፎቶዎች አሉት። ተቀባብቶ፣ ቀሚስ ለብሶ፣ ሂል ጫማ ተጫምቶ አንዳንድም ቪዲዮዎች ላይ በአወራሩ እና በአቀራረቡ የሴት ድምፅ እና አነጋገር እንዳለው አየሁ።

> “
>
> **የማውቀው ሰው ቢሆንስ? ወንድሜ አህቴ ቢሆኑስ? ልጄ ቢሆንስ? ዝም አላከሁ? አውነት ከልጄ የማስበልጠው ነገር የማልረዳው ከአእምሮዬ በላይ የሚሆን ሀሳብ አለ? የለም።**

ከሁሉ ግን ውጪ ሀገር ላይ የኢትዮጲያን ባንዲራ ይዞ የጌዮች ስላማዊ ሰልፍ ላይ እንደተሳተፈ ሳይ ቅር አለኝ። ሀገር የማሰደብ እና የመናቅ ስሜት ተሰማኝ። ከዛ በፊት የሀገር እና የወገንተኝነት ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም ነበርና ራሴን <<የምን ወገኝነት ነው?>> ብዬ ተቆጥቼ ከፔጁ ልወጣ ስል አንድ ጥያቄ ጭንቅላቴ ውስጥ ቀረችብኝ። ጥያቄውም  ማን የጋራ ጓደኛ ቢኖረን ነው ይሄ ልጅ ሰተት ብሎ ታይም ላይኔ ላይ የመጣው? የሚል ነበር። ወዲያው የጋራ ጓደኞችን ማየት ጀመርኩ አብዛኞቹን አላውቃቸውም ለሰከንድ ሳላወላውል ብሎክ ወይ ኧንፍሬንድ ለማድረግ አልተቸገርኩም። አንዱን ግን አልቻልኩም። ይህ ሰው በቅርብ የማውቀው፣ የማከብረው፣ በሚፅፋቸው ፅሁፎች ምክንያት እንድወደውና እና እንድከታተል ካደረጉኝ ሰዎች መሀከል ዋነኛው ነበር።  ብዙ ጥያቄዎች በውስጤ ይመላለሱ ጀመር። ስለ ይሄ ሰው ያለኝን

መረጃዎች አእምሮዬ ከዚህም ከዛም እየለቃቀመ ያገጣጥምልኝ እና ጌይ ነው  ብሎ ወደሚያሳምን መደምደሚያ አስጠጋኝ። መቀበል ግን አለፈለኩም። ዝምብዬ አለባብሼ ላልፈው የምችለውም ርእስ እንዳልሆነ ተረዳሁት። ስለዚህ ማድረግ የምችለው ሰውዬውን በግል ማግኘት እና ጥርጣሬዎቼን በማስረጃ መደገፍ ነበር። ጥሩ ፀሀፊ አይደለሁም። እንዲሁ የመጣልኝን አጫጭር እና ፊልተር ያልተደረጉ ነገሮች የምፅፍ እንጂ ግን ከዚህ ሰው ጋር ሊያግባባኝ የሚችለው አንድ ምክንያት እሱ ነበርና ደህና የምለውን መርጬ እንዲያነብልኝ እና አስተያየት እንዲሰጠኝ በድፍረት መልእክት ላኩለት።

እሱም አላሳፈረኝም አንብቦ መስመር በመስመር ያለኝን እንከን ከስርአተ ነጥብ ጀምሮ እንዳስተካክል አስተያየቶችን አስፍሮ ላከልኝ። አአምሮዬ በዚህ ፍጥነት አንብቦ አስተያየት ሰጥቶ መመለሱን ጥሩ ሰው አስብሎ ብቻ መቀበልን አልፈለገም። እንከን እየፈለግኩ ስለነበር ምስጋናዬን እንደሚገባው ሳይሆን ለብ አድርጌ መለስኩለት። ራሴንም በጥያቄ አፋጠጥኩ

<<እሺ እንዳሰብሺው ጌይ ቢሆንስ? ካንቺ ህይወት ጋር ምን አገናኘው?>>

<< ምን.. ም..   እኔንጃ.. ለምን አያገናኘውም ... ያገናኘዋል እንጂ እናት ልትሆኚ ነው። ያውም የወንድ ልጅ። ቀድሞ ከመጡ ከኋላ ላለው ተከታይ ሁልጊዜም አጥጋቢ መልስ ማዘጋጀት ውዴታ ሳይሆን ሀላፊነይ ነው። ኮረኮንቻችንን መደልደል አረማችንን ማጥራት ሁላችንም ልንሰራው የሚገባ የቤት ስራ ነው ስለዚህ ስየቤት ስራሽን ባግባቡ ስሪ!>> የሚል መልስ ከራሴ አገኘሁ። በኢነርጂ አምናለሁ። በቀላሉ ያንድን ሰው በጎ ወይንም የሚጋፋ ሀይል ማንበብ እችላለሁ። ..የማይፈርስ የማያስደርስ ወታደራዊ ሀይል  ያለው ከባድ  ኢነርጂ ተሸክሞ የሚዞር አለ። ቀላል፣ ነፃ፣ በጎ፣ ኢነርጂ ያለው ሰው አለ። ይሄን ሰው በአካል አላውቀውም

ቢሆንም ከእሱ ጋር ያለን የመንፈስ ግንኙነት እጅግ በጣም ቀላል እንደሆነ ተረድቼዋለሁ። በቂ ምስጋና ስላልሰጠሁት እንዳልተሸበረም፣ የክብር ይገባኛል አይነት ከባድ ኢጎ እንዳልነበረበትም ተሰምቶኛል። ስለዚህ በሌላ ርእስ ወደ ኢንቦክሱ ሄድኩ። ብዙ አወራን ተወያየን። ብዙ የጋራ የምንወዳቸው ነገሮች እንዳሉን አወቅኩ። ዋናውን ጥያቄዬን ገሸሽ አድርጌ ለረጅም ግዜ በተለያዩ ርእሶች ላይ ብዙ ነገር አወራን። አንድ ቀን ደፍሬ ከተመቸው ቡና እንድጋብዘው ጠየቅኩት። እንደውም በተለየ እሱ ራሱ ቡና እንደሚያፈላልኝ ተስማምተን ቤቱ ተገናኘን።

አእምሮዬ ውስጥ <<በቃ ጌይ ነው!>> የሚል ድምዳሜ << አዎ ነኝ!>> የምትል የራሱ ማረጋገጫ ስትቀር ስላዘጋጀሁ ቤቱ ለመሄድ አልፈራሁም። እንዲሁም ከእሱ በሚደርሰኝ ቀለል ያለ የጥሩ ጓደኝነት ኢነርጂ እና በእርግዝናዬ ምክንያት ገዛ ቤቱ ሰትተ ብዬ ለመሄድ አላንገራገርኩም።

ያንለት ቤቱ እንደደረስኩ ሞቅ ባለ አቀባበል ተቀበለኝ። ብዙ አወራን ተጨዋወትን ስለፊልሞች ስናወራ ሆን ብዬ በአሁን ግዜ በየፊልሙ ስላሉት ጌይ ካፕተሎች አነሳሁ። እሱም መለሰልኝ - እንደውም ካልሽ ዘገየ .. በአሁን ሰአት በየፊልሙ ምናብ ብቻ ሆኖ አልነበረም መቅረት የነበረበት። በእውነታውም አለም መቀበል እና ሰዎች የፍላጎታቸውን እንዲኖሩ መኖር ነበረበት። ይሄ እኮ የተፈጥሮ መብት ነው። የሚገርመኝ ነገር ሌላው ደግሞ ለአዲስ ነፃ ሀሳብ ሲሚገቱ ለውጥ ለማምጣት ሲጥሩ አሁንም በየፊልሙ ሆሞሴክሹዋሊትን እንድንቀበል ሲረዱን የሚጠቀሙት ወንዶቹን ብቻ ነው። ሌዝቢያኖቹስ? አይገርምሽም? Gender discrimination በአዲስ ፎርም ይልሻል ይሄ ነው። አለኝ። አንዱን ርእስ በስርአት ፕሮሰስ ሳላደርገው ወደሌላ ርእስ አሻገረኝ። ቀስ እያለ ከበፊት ከኦሪት ግዜ ጀምሮ ስለነበረው ሆሞሴክሹዋሊቲ አባቶቻችን በጦርነት ግዜ ያውም በሀይል ያለፍቃድ ስለሚያደርጉት ከወንድ ጋር ግንኙነት እና ስለ ስብሀት መፅሀፍ ሰባተኛው መልአክ ከቡና ጋር እያዋዛ አወጋልኝ። ስለግል ህይወቱም ጥርጣሬዬን ከንቱ ያደረጉ ፋክቶች አጫወተኝ።

ያን ለት ቤቴ ስሄድ የስብሀትን መፅሀፍ ተበድሬ ውስጤ ያለ አዲስ ማንነት ፈንቅዬ ካልወጣሁ እያለ እየታገለኝ ነበር።

አየለ ነብሮ የስብሀት ካራክተር ነው። ቁጡ ግልፍተኛ ያደገበት ን ማህበረሰብ የሚጠላ ሴት የማይቀርብ ብዙ በትክክል ያልተገራ የስሜት ኮተቶች የተሸከመ ሰው ነው። በፈረንሳይ ሀገር ትምህርቱን ሊማር ሄዶ ከንጭንጭ እና ከትምህርት የተረፈውን ግዜ በፖለቲካ ላይ ሲነታረክ የሚያሳልፍ ሰው ነበር። ከጓደኞቹ መሀል የመናዊ ጓደኛው ያሲን ብቻ ነበር አየለ ፍላጎቱ በፆታ ተመሳሳዮቹ ወንዶች እንደነበር ያወቀበት። ያሲን ይሄንንም በተረዳበት ወቅት አየለ በብዙ ብስጭት እና ራስን ካለመቀበል ቴንሽን በመጣ ድብርት የአእምሮ ህመምተኛ ሆነ ። የነበረበት ብቸኝነት የሚያሳዝን ነበር። በማህበረሰብ እና በራስ ግንዛቤ ማነስ ሌላውንም ሰው ራሱንም ሲጠላ ቆይቶ በመጨረሻም የዘገየ መልስ አላዳነውምና ከነስቃዩ ህይወቱ አለፈ።

የማውቀው ሰው ቢሆንስ? ወንድሜ እህቴ ቢሆኑስ? ልጄ ቢሆንስ? ዝም እላለሁ? እውነት ከልጄ የማስበልጠው ነገር የማልረዳው ከአእምሮዬ በላይ የሚሆን ሀሳብ አለ? የለም።

<<የእናንተ የሀበሾች ኑሮ ወንድ ለወንድ መዋደድን በጣም ከመጥላቱ ከመናቁ የተነሳ ተራው ሀበሻ ወንድ ለወንድ መዋደድን እንደ ትልቅ ሀጢያት፤ እንደ ዋና ውርደትና እንደ ቀፋፊ እፍረት ይቆጥረዋል።>> ገፅ 30 ሰባተኛው መልአክ

መፅሀፉን ከድኜ ብዙ አሰብኩኝ። ከዚህ መፅሀፍ በኋላ አውቃለሁ በቅቻለሁ ላለማለት ወሰንኩ። የሰው ልጅ ተፈጥሮው ሰፊ ነው የምናውቀው ጥቂቱንና በብዙ ተሞክሮ የቀለለልንን ነው። የማናውቀው ሰፊ ተፈጥሮ እንዳለን ይሰማኝ ጀመር።

**የሰው ልጅ ተፈጥሮው ሰፊ ነው የምናውቀው ጥቂቱንና በብዙ ተሞክሮ የቀለለልንን ነው። የማናውቀው ሰፊ ተፈጥሮ እንዳለን ይሰማኝ ጀመር።**

# ፍቅር፣

## ማንነትን ማሳሰብቅ እና ፍርሃት





“

**የነገሩ ፍሬ ነገር እንዲህ ነው፤ እኔና እሷ ፍቅረኛሞች እንደሆንን እንደሚያውቅና እሱ ያለኝን ነገር ካላደረኩ ደኅንነታችን አደጋ ላይ እንዳለ ነበር የነገራት።**

“ለሚስትሽ ብሬን እንድትሰጠኝ ንገሪያት”

ፍቅረኛዬ ለአምስት ዓመታት አብሬው ከሠራሁትና የሥራ ግንኙነቴ ከተቋረጠ ሰው የደረሳት የስልክ ጥሪ ነበር። በጣም እያለቀሰች ስለነበር የምትለኝን ነገር የተረዳሁት በተወሠነ መልኩ ነበር እናም ያለችበት መድረስ እስክችል ድርስ በስልክ እያወራኋት ቆየሁ። ከ15 ደቂቃ በኋላ ያለችበት ቦታ ስደርስ በጣም ተረብሻና መንቀጥቀጥ ማቆም እስከማትችል ድርስ እያለቀሰች ነበር።

ልይዛት አልቻልኩም ነበር። እሷ የሚያስፈልጋትንና እኔም እንደፈለኩት ዕቅፌንና ድጋፌን ልሰጣት አልቻልኩም ነበር። በዛ ሁኔታ ውስጥ ሁለት ሴቶች ለረጅም ጊዜ ተቃቅፈው መታየታቸው ትኩረት ሊስብ የሚችል ነገር ነበር፤ በጊዜውም ትኩረት የማንፈልገው ነገር ነበር። መኪና ውስጥ ሆነን ልንታዘዝ ወደምንችልብት ካፌ ሄደን ለመጠጣት ሃሳቡ’ንኳን ያልነበረንን ሻይ አዘዝን፤ ያው ያዘዝነው እንደዛ ባለ ፀጥታ ቦታ ማቆሚያ በመፈለጋችን ነበር። ከዛም ምን እንደተፈጠረ ለማወቅ ሞከርኩ።

አንድ ከኔ ጋር ይሠራ የነበረና ራሴን ግልጽ አድርጌለት የማላውቅ ሰው አንድ መልዕክት ለኔ እንድታስተላልፍልኝ ደውሎላት ነበር። የንግግሩ እንድምታ ግልጽ ነበር። የነገሩ ፍሬ ነገር እንዲህ ነው፤ እኔና እሷ ፍቅረኛሞች እንደሆንን እንደሚያውቅና እሱ ያለኝን ነገር ካላደረኩ ደኅንነታችን አደጋ ላይ እንዳለ ነበር የነገራት። ኢትዮጵያ ውስጥ የምትኖር የትኛዋም “ኩዊር” ብትሆን ትንሽም ቢሆን ራሷን ግልጽ ማድርግ የሚያመጣውን ዋጋ

> **ፍርኀቷ ይገባኛል እናም ልሸነፍላት ወሠንኩ። ለሱ በማስፈራሪያ ሊያገኘው ላሰበው ጥቅም መሸነፍ ግን ደሜን ነው ያፈላው። ጊዜ ወስጄ በጥሞና ማሰብ ፈለኩ።**

መክፍል አትፈልግም።

ሁለታችንም የደወለላትን ሰው በደንብ እናውቀዋለን። አብሬው አምስት ዓመት ገደማ ሠርቻለሁ። አብረን ከመሥራታችን በፊት አንዳችን የሌላኛችንን ቤተሰብ በደንብ እናውቃለን እናም አንዳንዴ ሰው እኅትና ወንድም እንመስለዋለን፤ ብዙውን ጊዜ ትክክል እንዳልሆኑ ማስተካከሉ ግድ አይሰጠንም። የሥራ ግንኙነታችን የተቋረጠው በፈጸመው አንድ የሥነ-ምግባር ጉድለት ተግባር ነበር፤ ለሥራው ስንብት የተከፈለው ክፍያ የተሰላበት መንገድ ፍትሸዊ አይደለም የሚል ስሜት አለው። የኔ አቋም ደ'ሞ የስንብት ክፍያ "ፍትሐዊነት" አይደለም፤ ይልቁንም በኢትዮጵያ የሠራተኛ ዐዋጅ አግባብ የሚሰላው ቁጥር እሱ እንደሚፈልገው ዓይነት ውጤት ስላላስገኘለት ነው።

ለሷ ከመደወሉ ከቀናት የስንብት ክፍያውን ተቃውሞና አስፈራርቶኝ ነበር ጥሎኝ የሄደው። በረድ ብሎለትና ወደቀልቡ ተመልሶ ነገሩን እንጨርሰዋለን በሚል እየጠበኩ ነበር። ማስፈራራቱ እንዳለ ሆኖ ለፍቅረኛዬ ይድውላል ብዬ አልጠበኩም ነበር። በርግጥ ምንም እንኳን በድርጅቱ ውስጥ ያለው ጊዜ እያበቃ እንደሆነ የነገርኳት ቢሆንም በመኻላችን ስለተፈጠረው አለመግባባት ግን ያን ያህል ቁብ ያለው ነገር ነው ብዬ ስላላሰብኩ አልነገርኳትም ነበር። ሁል ጊዜ ማለት በሚቻል ሁኔታ ምሳ አብሮኝ ስለሚበላና አንዳንዴ ምሳ ላይ ወይም ከምሳ በኋላ ተቀላቅላን ሻይ/ቡና አብራን ስለምትጠጣ በደንብ ታውቀው ነበር። እኔና ፍቅረኛዬ ጠንቃቃ እንደሆንንና ድርጊታችንም እሳልፎ ሊሰጠን በሚችል ሁኔታ አይደለም ብዬ አስብ ነበር። እጅ ለእጅ አለመያያዝ፣ ዓይን ለዓይን አለመፋጠጥና አንዳችን የሌላኛችንን ንግግር አለመጨረስ። ጥሩ ሴት ጓደኛሞች ከመሆን የዘለለ ነገር እንዳይወሰድብን እንጠነቀቅ ነበር። ምንድን ነው ያሳጣን? ይመስልኛል ምንም ያህል ቢሞከር ፍቅርን መደበቅ አይቻልም።

መኪናው ውስጥ ለሁለት ሰዓት ተቀመጥን። ስታለቅስ ዐየኋትና በቃላት ብቻ ላረጋጋት ሞከርኩ። ከጭንቀቷና ከፍርኀቷ የምትጽናና አልሆነችም። በአስፈላጊው ሰዓት ዐቅፌ ልንከባከባት አለመቻሌና ችግር ውስጥ ስለከተትኳት የተሰማኝ የጥፋተኝነት ስሜት ልቤን ሰበረው።

መፍትሔ እንደምናገኝለት ላሳምናት ሞከርኩ። በርግጥ በሰዓቱ ግጭት መፍትሔ አይሆንም የሚለው እኔነቴ ቁጣውን ሊገልጽለትና ሰውነቱ ላይ ጉዳት ሊያደርስበት ዝግጁ ነበር። ለዛ በላይ ግን በራሴ ተናድጄ ነበር። ሁኔታችንን እንዴት አልተከታተልኩም? እንዴት ይህንን ሰው እንደቤተሰቤ ላስበው ቻልኩ? ምን ባስብ ነው ከዚህ ሰውዬ ጋር ሆኜ ለሻይ ቡና እንድትቀላቀለን አዘውትሬ እሷን መጋበዜ? እንዴት ከሚገባው በላይ ሕይወቴ ውስጥ እንዲገባ ፈቀድኩለት?

በርግጥ አንዱ ጸጸቴ ለችግሩ መፍትሔ አይሆነኝም። ማውራት በምትችልበት ደረጃ ስትረጋጋ እንደ`መፍትሔ ብናደርጋቸው ብዬ ያሰብኳቸውን መደርደር ጀመርኩ። በንግግሬ መኻል አቋረጠችኝና "እባክሽ የፈለገውን ያህል ክፈይው" አለችኝ።

ፍርኀቷ ይገባኛል እናም ልሸነፍላት ወሠንኩ። ለሱ በማስፈራሪያ ሊያገኘው ላሰበው ጥቅም መሸነፍ ግን ደሜን ነው ያፈላው። ጊዜ ወስጄ በጥሞና ማሰብ ነበረብኝ። ባለኝ ሥነ-ምግባርና እንደ አንድ አቋም እንዳለው ሰው እንደዚህ ላለው ሥነ-ምግባር ለጎደለው ነገር የመሸነፉ ሃሳብ በትንሹም ቢሆን የመሞት ያህል ነው።

በደንብ ታውቀኛለችና ያመጣችው የመፍትሔ ሃሳብ ውስጤ ተረጋግቶ እንደማይቀበለው ይገባታል፤ ስለዚህ ተማፀነችኝ። ቤተሰቦቼ የሚያውቁትና የሚደግፉኝ ስለነበሩ ለቤተሰቦቼ ግልጽ መውጣቴ ለኔ የሚያስጨንቅ ነገር አልነበረም። ለሷ ግን ለቤተሰቦቿ ግልጽ መውጣት የምርጫ ጉዳይ አይደለም። ደንበኛ የኢትዮጵያ ወላጆች ዓይነት ነበሩ፤ ልጃቸው 30 ዓመት ሲሞላት ከወንድ ጋር ተጋብታ ብዙ ልጆች እንዲኖራት የሚጠብቋት።

ፍርኀቷ ተጨባጭነት ያለውና ጊዜ የማይሰጥ ነበር። ለሕይወቷ ነበር የፈራችው።

የኔም ፍርኀቴ የምር ነበር። ሁኔታው ከፍርኀትም ይልቅ መርኅን ዋጋ የሚሰጥ መልካም ሰው የመሆን ፍላጎቴን ምን ሊያደርገው እንደሚችል ፍርኀት ተሰማኝ።

በመጨረሻም ለፍርኀቷ ተሸነፍኩ እና ከራሴ ኪስ ከፈልኩት። ከዛ ቤተሰቡ ጋር በመሄድ በደፈናው ከሕይወቴ ሊርቅ እንደሚገባ ተናገርኩ። ብሩን ተቀበለና ራቀኝ።

እስኳሁን ድረስ ለራሴ ያለኝን ክብር አሳልፌ በመስጠቴ ራስን እወቅሰዋለሁ። ነገር ግን አንድ ሰው ፍቅር ወንጀል በሆነበት ሀገር ሲኖርና የአንድን ሰው ጉሮሮ በጠራራ ፀሐይ መቁረጥ እንደጀግንነትና እንደ ሀገር ፍቅር በሚወሰድበት ሀገር ሲኖር የሚከፍለው ዋጋ እንደሆነ እገምታለሁ።

# ቤተሰባችሁ ማንነታችሁን ብትገልፁላቸው ምን ይላሉ?

---

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

---

**Alfa Alfa**
የኔ ባልነግራቸውም መጠርጠራቸው አይቀርም😂

**Son Lucy 'S Essex**
**Eden Samuel** ይመስለኛል ከባድ ነው እንደየ ቤተሰብ የአመለካከት የአስተሳሰብ የጭንቅላት አቀባበል የሚለይ ይመስለኛል ከኔ ከደረሰብኝ አንግል ተነስቼ የቤተሰብ ሁኔታዎች ለመነገር በመጀመሪያ ቤተሰባቼ አመስግናለሁ 🙏 ማለት ያውቃሉ ግን ማንሳትም ማወራት በአጠቃላይ አለውቅም ከኔ ጀርባ ተማከረው እንደሆነ ይሄ እርስ በክፉም በደግሞ እኛ ቤት አይነሳም ቀሚል ቤተሰብ ስለኔ ያወቀበት መንገድ በገዛ ጓደኛዬ ነው ማለት በዚሁ በእኛ ላይ ያለ ጓደኛዬ የአሁኑ ×የቀድሞ ካፕሌ ነው በወቀቱ እኔ በእድሜ ልጅ ነበርኩኝ ብዙም በህይወት የሚደረጉ ጥንቃቄ ሴኩሪቲ የሚደረጉባቸው ነገሮ እወቀት አልነበረኝ ቤተሰብ ደረጃ አስተዋቅሁት ከቤተሰብ ጋራ ከኔ በበለጠ ተቀባይነት ተወዳጅነት አተረፈ ሆኑም እኔ ብዙ ነገሮች እያወቅሁ በላይ የሚደረጉ ነገሮች ስራዳ መለያት አመራጭ አደረኩ ይህን ወሳኔ ለመስቀየር ታቅዳ ነበር ለቤተሰብ የተነገረው 🤷‍♂️ እና በወቅቱ ከባድ ነው ከእናቴ ወጪ የተረጋጋና ነገሮች ለማብረድ የሞከረ ሰው አልነበረም በተለይ እህቶቼ አንደኛው እህቴ በተደጋጋሚ እገልሀለው የሚል ዛቻ ነበር ወንድሞቼ ጋራ ባዩኝ ቁጥር የተሰበረ ልብ ነበር የማይባቸው እናቴ ግን በጭራሽ እኔ ፊት ህመሟን ለመደበቅ ምንም እንዳለተፈጠረ ለማስመሰል ትጥር ነበር እኔ በአጠቃላይ ቤታች ለኔ ሲኦል ነው የሆነብኝ ከቤት እንዳልወጣ እገዳ ቢደረግብኝ ተደብቄ በምሽት ከቤት ጠፋሁ ብዙ ዋጋ ከፈያለሁ ሆኑም በእናቴ ጥረት እስከዛሬ ምን እንደተመከሩ ባለውቅ ወደቤት ተመለሻለሁ ሁሉም ይቅርታ ጠይቀውኛል ሰላም ነኝ በጭራሽ የቀነሰብኝ ነገር የለም ከወንድሞቼም ከእቶቼም ከእናቴም አባቴ በህይወት ስለሌላ አለቅ ቢኖር ምን ሊከሰት እንደሚችል እኛ ቤት ይህው ስለ ተመሳሳይ ፆታ በክፉም በደግም ማንሳት በህግ የተከለከለ ከሁነ እረጅም አመታት አስቆጥሯል

**ላያስችል አይሰጥም**
ምላሹ በጣም ከባድና ሀላፊነት የሚጠይቅ ይመስለኛል፤ ለእናቴ ጌይ ነኝ ብላት her first question will be "ጌይ ምንድነው?" have you seen this much she do not have enough awareness. ግን ደፍሬ ካብራራዉላት ትታመምብኛለች ልትሞትብኝም ትችላለች። an other side አባቴ ሽጉጥ ሊመዝብኝም ሆነ "ዓይንህን አልየው" ሊለኝ ይችላል።

ሆኖ ካላዩ እርግጠኛ መሆን አይቻልም!

# ቤተሰባችሁ ማንነታችሁን ብትገልፁላቸው ምን ይላሉ?

---

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

---

**Samri Sam**
እኔ እንዲ ነኝ ብዬ ከተናገርኩ መጀመሪያ ለራሴ አሬሳ መገነዣ እንዲሁም ሳጥን ገዝቼ መስቀመጥ አለብኝ ሆ እንዲህ ከመሆን ፈጣሪ ይሰውረኝ 😉😌

**በፍቅር ይሁን**
እሰይይይይ አስካለ😂😂😂
እየመጣሽ ተኚ😂😂😂😂
በጣም አደገኛ የሚባል ግርምትና ትርምስ እንዲሁም መሸማቀቅን የሚያስተናግድ ቤተሰብ ነው ያለኝ። እኔን ለመቅረፅ በጣም ደክመውብኛል በብዙ መተማመን ተደግፈውብኛልም!!! ይህ የኔና የማፈቅረው የቤተሰቤ መሰራት ነው። ተፈጥሮዬን አስረድቼ ከማገኘው የአመታት ነፃነት ይልቅ ሲሰሙ የሚሆኗት ነገር ትከብደኛለች። ከዚህ ሊረዱት ከማያስቡት ስሜቴ ይልቅ አብረን የመጣንባቸው የጋራ መኖሮችን አከብራቸዋለሁ። እንኳን ከእነርሱ ከየትኛውም ፍጥረት ጥላቻና መተውን የማስተናገድ አቅምና ፍላጎት የለኝም። አኗኗሬ በሐይማኖት እና ቤተሰባዊ እንዲሁም ማህበረሰባዊ ምግባርና ስርአት ታሽቶ የኖረ በመሆኑ የኔ መገለጥ የሚጎዳው እኔን ብቻ አይደለም። በገዛ አረዳዱ የሚያጎነብስ ስብስብ መሀል ነኝ እና ተሸሽጎ መኖርን ተቀብለው ከሚኖሩ የስሜት ሰዎች መደብ ነኝ።
እንደአረዳድ....
ከወንድ ጋር ያለኝን የፍቅር ወይም የስሜት መንገድ አክብጄ ወይም አሳንሼ አላየውም። ዘና ስል ለሁለታችንም ደህንነት ተጠንቅቄ በክብርና ትኩረት እሆነዋለው። ያየኝ እስኪለየኝ ድረስ ትኩረት ለመሳብ አልጋጋጥም። ለማደር ወይም ለመከረም ስፈልግ ቤተሰብ መስማት በሚፈልገው ቃል ይነገረዋል።
ለእኔ ሰላም ሆኖ መኖር የቤተሰቤ እኔን ወዶ መኖር ዋስትናዬ ነው። ቤተሰቤንና ወንድዬን በሁለት ቦይ በማፍሰስ ነው ፍቅራቸውን ወደ ውስጤ ማሰርገው 🖐🙏

**Jamzee King**
I can come out to anyone bt never to any of ma family member

we all kn our society እና ካወቁ ያብዷሉ n they might be try to k*ll me

# ቤተሰባችሁ ማንነታችሁን ብትገልፁላቸው ምን ይላሉ?

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

**ሄኖክ በፍቅር**

እኔ ለታላቅ ወንድሜ ለማውራት አስቤ አውቃለው እሱ በጣም ጥሩ የሆነ የመረዳት ብቃት አለው በብዙ ነገሮች አስተውዬዋለው እና በደምብ አድርጌ ባስረዳው እንደሚረዳኝ በጣም እርግጠኛ ነኝ !
ግን ይጎዳብኛል ብዬ እፈራለው ይሄን ስቃይ ምን በወጣው የሚጋራኝ
ደሞስ ነግሬው ምን አይነት ለውጥ ይመጣል መናገሬ ምን ሊጠቅመኝ ይችላል ? ብዬ አስብና አለማወራትን እመርጣለው የሚሰጠኝ ሀሳብ ሊኖር ይችላል ግን ታናሽ ወንድሙ እንዲህ በመሆኑ በጣም እንደሚያዝን እንደሚጎዳ አስባለው ስለዚህ አለመናገርን መርጫለው

**Nahi Gay**

እኛ ሀገር ላይ እማይ አይመስለኝም የሆነ ተአምር ተፈጥሮ እንኳን ቢከበር ህዝቡ ዱንጋይ እና ዱላ ይዞ ሚያባርረን ነው ሚመስለኝ ያለው ጥላቻ ከባድ ነው አንዴ ከቤተሰብ ጋር ስለኛ ጉዳይ ወሬ ተጀምሮ የተሰጡትን አስተያየቶች ሳስባቸው ይከብዱኛል ከተሰጡት የመፍትሄ ሀሳቦች መሀል አንዱ ሰብስቦ ማቃጠል እሚለው ነበር አሁን ድረስ ሳስበው ጆሮዬ ላይ ያቃጭላል እንደው ይሄን ፍርድ ከፈረዱባቸው መሀል አንዱ እኔ የነሱ የቤተሰብ አባል እንዳለው ቢያውቁ እንዲ ይሉ ነበር ብዬ ሳስብ ደሞ
አንዳንዴ ከሀገር የመውጣት ፍላጎቴ በድንገት ሚጨምረው ለዚ ይመስለኛል አንድ ቀን ግን ከሀገር ውጪ ካሉ መሰሎቼ ጋር እማከብር ይመስለኛል Proud Gay እሚል ቲሸርት ለብሼ በቀኝ እጄ ደሞ ባንዲራችንን ይዤ እና ምወደውን ቀንጆ አጭር የጅንስ ቁንጣ አርጌ 👭👬❤️

**Ordinary**

ቤተሰብ ብዬ የምጠራቸው ለኔ የቅርብ የሆኑ ሰዎችን ብቻ ነው እነሱም: እናት፣ አባት፣ እህት እና ወንድም። ከሌሎች የቤተሰብ አባላት ጋር ብዙም ቅርበት ስለሌለኝ ዘመድ ነው ምላቸው።

ቅድሚያ ላስቀመጥኳቸው የቤተሰቤ አባላት ስለ ተመሳሳይ አፍቃሪነቴ ብነግራቸው የሚኖራቸው ምላሽ በዝርዝር ባስቀምጠው ...

እናቴ :- በህይወት ስለሌለች የሷን ልለፈው።

አባቴ:- መጀመሪያ እንደነገርኩት የሚገባው አይመስለኝም። ቢገባውም የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር ምን ማለት እንደሆነ ሳይገባኝ የቀባጠርኩ ነው ሚመስለው። ልክ የማወራው ነገር የእውነቴን እንደሆነ ሲረዳ ከክብሩ የሚበልጥበት ምንም ነገር ስለሌለ መጀመሪያ የኔን ህይወት ያጠፋል ቀጥሎም የራሱን ህይወት ያጠፋል።

ወንድሜ:- አንድ ወንድም ነው ያለኝ። በመሃከላችን ሰፊ የእድሜ ልዩነት ስላለ ብዙም ተቀራርበን የግል ጉዳያችንን አናወርም ስለዚ የሱን ምላሽ እርግጠኛ ሆኜ መናገር ቢከብደኝም ባህሪው ከአባቴ ጋር በጣም ስለሚመሳሰል ምላሹም ከአባቴ የተለየ ይሆናል በዬ አላስብም።

እህቶቼ:- ሁለት እህቶች ነው ያሉኝ። አንዳንዴ ሳስበው ሁለቱም ስለማንነቴ የሚጠረጥሩት ይመስለኛል። እርግጡን እኔ ብነግራቸው የሁለቱም ምላሽ ተመሳሳይ የሚሆን ይመስለኛል። ሁለቱም ለኔ ያላቸው ፍቅር አይቀንስም፣ አመለካከታቸውም አይቀየርም ነገር ግን ሁለቱም ለሃይማኖታቸው ጠንከር ያለ አቋም ስላላቸው “እንድፈወስ” የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። በተለይ ታላቋ እህታችን ላይ ጫናው ሚበረታባት ይመስለኛል። እናታችን በልጅነቴ ስላለፈች እሷ ነች ያሳደገችኝ ስለዚ እሷ ያጎደለችብኝ ስለሚመስላት እኔን ሳይሆን እራሷን በፆም እና በፀሎት የምትጎዳ ይመስለኛል።

ዘመዶቼ ሁሉም ማለት በሚያስችል መልኩ ራሳቸውን እንደቅዱሳን ስለሚቆጥሩ ምንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ ይላሉ ብዬ አላስብም።




## ምስጋና ለቤተሰብ

ውድ ቤተሰቤ:-

ከኩዊር ሰዎች መሃል ስሆን አብዛኛውን ጊዜ እንዴት ማንነቴን መቀበል ምንም እንዳልከበደኝ ከሚያወሩ ጥቂቶች ነኝ፤ ይሄም በእናንተ ምክንያት ስለሆነ አመሰግናለሁ።

አንድም ቀን የሀፍረት ስሜት እንዲሰማኝ አላደረጋችሁም። በቤት ውስጥ ስርዓተ ፃታ እና ወሲባዊነቴን አልተቆጣጠራችሁትም። ጎረቤትና ዘመድ በማንነቴ ዙሪያ እንዲያሳፍሩኝ ወይም ማንነቴን መቀየር እንዲሰማኝ እንዲያደርጉ ቦታ አልሰጣችኋቸውም። አላፊው አግዳሚው “ኖርማል” መሆን እንዳለብኝ ሲሰብኩኝ እነሱን ከመስማት ይልቅ ከጎኔ ቆማችኋል። ማንነቴን እንድፈትሽ እና እንዳድግ ፈቅዳችሁልኛል። እኔ ለእኔ በቂ እንደሆንኩ እንዲሰማኝ አድጋችኋል። በስተመጨረሻም ኩዊር ማንነቴን ስገልጥላችሁ አይናችሁን አላርገበገባችሁም። አይናቸውን ላርገበገቡብኝ እንኳን በኔ ቦታ በመሆና ተሟግታችሁልኛል።

የኩዊር መንግስተ ሰማያት ኢትዮጵያ ውስጥ ቢኖር፥ በእናንተ ደጋፊነት እና ፍፁም መቀበል እኔ እዛ እየኖርኩ ነው ማለት እችላለሁ። ሁላችሁም ብርታቶቼ ናችሁ። ኢትዮጵያ ውስጥ መኖርን መቀጠል የቻልኩት በእናንተ ምክንያት ነው። ይህን ስል ምንም ስራ የለብንም ማለት አይደለም፤ እኔንም ሆነ የኢትዮጵያ ኩዊር ማህበረሰብን ድጋፍ እንደምትቀጥሉ ተስፋ አደርጋለሁ።

አመሰግናለሁ ቤተሰቦቼ!

በፍቅር